አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 233 ሚያዝያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

«ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ ለማፍራት እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማስረከብ መንገዱን መጥረግ ይገባል»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ ለማፍራት እና የበለፀገች ኢትዮጵያን ለማስረከብ መንገዱን መጥረግ አስፈላጊ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አስገነዘቡ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢድ አልፈጥር በዓልን ምክንያት በማድረግ ወልድያ ከተማ የሚገኙትን የአገር መከላከያ ሠራዊትን የደቡብ፣ ምሥራቅ፣ 6ኛ እና 8ኛ ዕዞችን ጎብኝተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለመኮንኖች ባደረጉት ንግግር ዝግጁነታቸውን አጠናክረው በመቀጠል የማሸነፍ ዕድላቸውን እንዲያሰፉ፣ ድል አድራጊ ሰብዕናን እንዲገነቡ እና የስጋት ተጋላጭነትን እንዲቀንሱ አበረታተዋል።

ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ ማፍራት እና የበለፀገች ኢትዮጵያን ለማስረከብ መንገዱን መጥረግ እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያ ለሺህ ዘመናት ክርስትናና እስልምና በፍቅር የኖሩባት አገር ናት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ የኩራታችን ምንጭ ነውም ብለዋል።

ኢትዮጵያ የሚነገር ታሪክ ብቻ ሳይሆን የሚለማ መሬት እና የሚያለማ ሕዝብ አላትም ነው ያሉት።

ይህንን የተረዱ ጠላቶቻችን ልማታችንን ለማደናቀፍ እና

«ኃላፊነት የሚሰማው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ግሩም ገብሬ

ከተማ አስተዳደሩ በአንድ ቀን ብቻ ከ101 ሺ በላይ ለሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ አጋራ

ገጽ 4

መንግሥት ለሠራተኞች ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ለመወሰን የገባውን ቃል እንደማያጥፍ ገለጸ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የሠራተኞችን ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ለመወሰን የገባውን ቃል እንደማያጥፍ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ለሠራተኞች የኑሮ ሁኔታ መሻሻል እና በተለያዩ የሥራ ክባቢዎች የሚነሱ ቅሬታዎችን በዘላቂነት ለመፍታት ጥልቅ ጥናቶች እየተካሄዱ ነውም ተብሏል፡፡

መንግሥት የሠራተኞችን ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ለመወሰን የገባውን ቃል እንደማያጥፍ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፍሪያት ካሚል ገለፁ፡፡

ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ የዓለም የላብ አደሮች ቀን (ሜይዴይ) በትናንትናው ዕለት ሲከበር ባደረጉት ንግግር እንደገለፁት፤ መንግሥት የሠራተኞችን ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ለመወሰን የገባውን ቃል አያጥፍም፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በጥልቅ ጥናት ታይቶ ሊሠራ የሚገባው ስለሆነ ጥናቶች እየተከናወኑ ነው ብለዋል፡፡

የአነስተኛ ደመወዝ ወለል ጉዳይ ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ የሠራተኞች ታሪክ ተከድኖ ይብሰል ከተባሉ አጀንዳዎች ውስጥ አንዱ ነበር ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ ለውጡን ተከትሎ መንግሥት በአጠቃላይ የዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል፤ በተለይ ደግሞ የሠራተኞችን ሕይወት ለማሻሻል በወሰደው ቁርጠኝነት ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ውሳኔ ከነውርነት ወጥቶ የአደባባይ አጀንዳ ሆኗል ብለዋል፡፡

የሠራተኞች ዝቅትኛ የደመወዝ ወለል የሕግ ጉልበት እንዲያገኝ ተደርጎ ፀድቋል፡፡ ሆኖም ወደ ተግባር ለመግባት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፤ በዝርዝር ጥናትና በጥንቃቄ ላይ ተመርኩዞ መሠራት ስለሚኖርበት እንጂ ሥራዎቹ አልቆሙም ሲሉም አክለዋል፡፡

እየተሠሩ ያሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እንደተጠናቀቁ ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ እንሸጋገራለን ብለዋል ሚኒስትሯ፡፡

የሠራተኛውን ጥያቄ ለመመለስ መንግሥት ወደ ኋላ አይልም ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ ሠራተኛው የተለያዩ ጥያቄዎች እንዳሉት እናውቃለን፡፡ ጥያቄዎቹን ለመመለስ ከሠራተኞች እና ከአሠሪዎች ኮንፌዴሬሽኖች ጋር የበለጠ ተቀራርበን እንሠራለን ብለዋል፡፡ በሠራተኛውና በኮንፌዴሬሽኑ በኩል የተጠየቁ ጥያቄዎች አብዛኞቹ ቅድመ ሁኔታና ዝግጅት የሚፈልጉ መሆናቸውንም ገልፀዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪያት ገለጻ፤ ቀጣይነት ያለው የኑሮ መሻሻል እና ዘላቂነት ያለው የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች መካከል የሠራተኛና የአሠሪ የግንኙነት ሁኔታ አንዱ ነው፡፡ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርም የተቋማዊ ለውጥ ሥራው አንድ አካል አድርጎ ይዞታል፡፡

የአሠሪዎችና የሠራተኞች ግንኙነትን ለማዳበር ከአሠሪዎች ጋር ተያይዞ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት

መንግሥት ስሠራተኞች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል

የጋራ ግብረ ኃይሉ ዝግጅቱን አጠናቆ ተልዕኮውን በቁርጠኝነት እየተወጣ እንደሚገኝ አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢድ-አልፈጥር በዓል ያለምንም የፀጥታ ችግር ተከብሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ የጋራ ግብረ ኃይሉ ዝግጅቱን አጠናቆ ተልዕኮውን በቁርጠኝነት እየተወጣ እንደሚገኝ አስታወቀ። የጋራ ግብረ ኃይሉ የኢድ-አልፈጥር በዓል የመልካም ምኞት መግለጫ አውጥቷል።

በየትኛውም እምነት ውስጥ ተደብቀው እምነቱ ከሚፈቅደው ውጪ የተለያዩ ፀረ-ሰላም እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ቡድኖችንና ግለሰቦችን ሕዝቡ ከውስጡ አውጥቶ በማጋለጥ ለፀጥታ አካላት አሳልፎ በመስጠት የተለመደውን ቀና ትብብሩን አጠናክሮ እንዲቀጥልና አገራዊ ግዴታውን እንዲወጣ የጋራ ግብረ ኃይሉ ጥሪ አቅርቧል።

በአገር አቀፍ ደረጃ ባለፈው ሳምንት ተከብሮ ያለፈው የፋሲካ በዓል እና ከሰሞኑ በአዲስ አበባ ከተማ የተዘጋጀው ታላቁ የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሃ ግብር በሰላማዊ መንገድ መካሄዱን አስታውሷል መግለጫው።

በመሆኑም ከጥምር የፀጥታ አካላት የተሰጠውን መመሪያ ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ላደረጉ የሁሉም ሃይማኖት አባቶች፣ በዓሉን በኮሚቴነት ላስተባበሩና ለመሩ አካላት፣ ምዕመናኑን በማስተናገድ ከፍተኛ ድርሻ ለተወጡ ወጣቶችና ሰላም ወዳዱ የአገራችን ሕዝብ እንዲሁም በዓላቱ በሰላም እንዲጠናቀቁ የራሳችሁን ድርሻ ላበረከታችሁ የፌዴራልና የክልል የፀጥታና ደህንነት ኃይሎች በሙሉ የፌዴራል የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል ምስጋና አቅርቧል፡፡

ልክ እንደ ፋሲካ በዓል እና የኢፍጣር መርሃ ግብር ሁሉ የኢድ-አልፈጥር በዓልም በተመሳሳይ ያለምንም የፀጥታ ችግር በሰላም እንዲጠናቀቅ የጋራ ግብረ ኃይሉ ዝግጅቱን አጠናቆ ተልዕኮውን በአዲስ አበባና በሌሎች የአገራችን አካባቢዎች በቁርጠኝነት እየተወጣ ይገኛል ሲልም ጠቅሷል፡፡

ይሁን እንጂ መንግሥት ለበዓላቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ባለበት በዚህ ወቅት ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ አንዳንድ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ሕዝቡን ለማሳሳትና የእምነቶቹ ወግና ሥርዓት ከሚፈቅደው ውጪ ምዕመናኑን ወደ ግጭት ለማስገባት እንቅስቃሴ እያደረጉ እንዳሉ የጋራ ግብረ ኃይሉ እንደደረሰበት አስታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ ከቀብር ቦታ ጋር በተያያዘ በተወሰኑ የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት የተነሳ ግጭት የተቀሰቀሰ ቢሆንም ግጭቱን በሃይማኖት ሽፋን ለማባባስ የሚደረገው ጥረት እኩይ ዓላማ ላላቸው ፀረ-ሰላም ኃይሎች ዕድል ስለሚፈጥር ሁሉም የሃይማኖት ተቋማት ይህንን ተገንዝባችሁ አጥፊዎችን ለሕግ ለማቅረብ እየተሠራ ያለውን ተግባር

ማገዝ ይጠበቅባችኋል ብሏል በመግለጫው።

በተመሳሳይ በስልጤ ዞን በወራቤ ከተማ ግጭቱን ለማባባስ በተናበበ በሚመስል አኳኋን በቤተ እምነት ላይ የደረሰው ቃጠሎ እና በክቡር የሰው ልጅ ሕይወት ላይ የደረሰው ሞት የክርስትናንም ሆነ የእስልምናን እምነቶች የማይወክል ተግባር እንደሆነም አንስቷል።

በጎንደርና በወራቤ ከተሞች በጠፋው ክቡር የሰው ልጅ ሕይወት እና በእምነት ተቋማቱ ላይ በደረሰው ውድመት የጋራ ግብረ ኃይሉ የተሰማውን ኀዘንም ገልጿል፡፡

ከዚሁ ሁከትና ብጥብጥ ጋር በተያያዘ ከሁለቱም ወገን በድርጊቱ ውስጥ የተሳተፉ እንዲሁም ከጀርባ ሆነው ግጭቱ እንዲባባስና ወደ ሌሎች የአገራችን አካባቢዎች እንዲዛመት ሲቀሰቅሱና ሲያነሳሱ የነበሩትን ፀረ-ሰላም ኃይሎችን የጋራ ግብረ ኃይሉ እያደነ ለሕግ ማቅረቡን እንደቀጠለም በመግለጫው ላይ ተነስቷል፡፡

አቶ ጃንጥራር አባይ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ አቶ መላኩ አስበል

«ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ በአዲስ አበባ ተጀመረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ታምርት በሚል መሪ ቃል የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለማሳደግ የተዘጋጀው የንቅናቄ መድረክ በይፋ ተጀመረ፡፡

ትናንት በአዲስ አበባ በጀመረው የንቅናቄ መድረክ ላይ የተገኙት ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፤ ተሰፍሮ የማያልቅ ተፈጥሯዊ ሀብትን በታደለችው ከመቶ ሚሊዮን በሚልቀው የሕዝብ ቁጥሯ ውስጥ አብዛኛው በአምራች ዕድሜ ክልል በሚገኝባት ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነን ተባብረን ከሠራን በአጭር ጊዜ ብልፅግና ላይ መድረስ እንችላለን ብለዋል። ብልፅግና ያለ አድካሚ ሥራና ጥረት ከቶውንም ሊሳካ አይችልም ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በአገራችን ከተሞች ለሥራ ፈላጊዎች የተለያዩ አማራጮችን ለማመቻቸት የከተሞችን የሥራ ዕድል ማጠናከር እና የተቀናጀ የኢንዱስትሪ ድጋፍን ማከናወን ለነገ የምንለው ተግባር አይደለም ዋና አጀንዳችን ነው ብለዋል፡፡

የሥራ ዓይነት ሳያማርጡ፤ ለሰማያዊና ነጭ ኮሌታ ክብር ሳይጨነቁ ወገባቸውን ጠበቅ አድርገው የሠሩ የደረሱበትን ከፍታ አይተናል ያሉት ከንቲባዋ፤ የሥራው መዳረሻ አላማው የሥራ ክቡርነትን ባህል በማድረግ፤ የማምረትና የአገር ውስጥ ፍጆታን ከመሸፈን ባሻገር የዓለም ገበያ ውስጥ በብቃት መግባትን መሠረት ያደረገ ነው ብለዋል። በተጨማሪም ለኢንዱስትሪው የምናደርገውን ድጋፍ በመፈተሽ አዳዲስ አሠራሮችንም በመተግበር የተሻለ ውጤት እንደምናስመዘግብ እምነቴ ነው በማለት የከተማ አስተዳደሩ ያለውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ በበኩላቸው፤ የሚሠሩ እጆችን ከሥራ ጋር ለማገናኘት በከተማዋ ከተያዘው እቅድ አንዱ «ኢትዮጵያ ታምርት» የሚለው ንቅናቄ አንዱ መሆኑን አንስተው፤ በዚህም ከዘርፉ በአመት የሚገኘውን ምርት ከፍ ለማድረግ ይረዳል ብለዋል።

ከተለመደው መንፏቀቅ ለመውጣት የተለየ ንቅናቄ ያስፈልጋል ያሉት ኃላፊው፤ ለዚህም አገር ውስጥ ምርት መሻሻል እና የሥራ ባህልን ማሳደግ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነው ብለዋል፡፡

ንቅናቄው በአሁኑ ጊዜ ካሉ 10 ሺህ 500 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ቁጥር ወደ 22 ሺህ ለማሳደግም እንደሚረዳ ነው የጠቆሙት።

በተጨማሪም ያለ ኢንዱስትሪ ልማት ያደገ አገር አለመኖሩን ያነሱት አቶ ጃንጥራር ዐባይ፤ «እኛም እንደ አገር ለመበልፀግ የተለያዩ ፖሊሲዎችን አሻሽለን ከኢንዱስትሪያሊስቶች ጋር ተቀራርበን መሥራት አለብን» ብለዋል።

የኢድ በዓል ገበያ በአቅርቦትና ግብይት የተቀዛቀዘ መሆኑን ነጋዴዎችና ሸማቾች ገለጹ

ሙሳ ሙሐመድ፣ በኃይሉ አበራና መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- የኢድ በዓል ገበያ በአቅርቦትና ግብይት የተቀዛቀዘ መሆኑን ነጋዴዎችና ሸማቾች ገለጹ፡፡

በአፍሪካ ትልቁ ገበያ ማዕከል በሆነው መርካቶ የኢድ ገበያን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሪፖርተሮች ተዘዋውረው ያነጋገሯቸው ነጋዴዎችና ሸማቾች የኢድ በዓል ገበያ በአቅርቦትና ግብይት ተቀዛቅዟል፡፡

በመርካቶ የቅመም ተራ የተለያዩ የቅመማቅመም መሸጫ መደብሮች ባማረ መልኩ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን አንድም ከላዩ ላይ የተነኩ ወይም የተሸጡ አይመስሉም፤ ለውበት የተቀመጡ ጌጦች በሚመስል ሁኔታ በማዳበሪያ አፍ ጢም ብለው ሞልተው ይታያሉ።

በመርካቶ ገበያ ግብይት የቅመማቅመም ነጋዴው አቶ ሳሚር ሽኩር እንደገለጹት፣ የኢድ በዓል ገበያ በአቅርቦትና ግብይት ተቀዛቅዟል፡፡

እንደ አቶ ሳሚር ገለጻ፣ የበዓል ገበያው መቀዛቀዝ ሊከሰት የቻለው ከፋሲካ በዓል ማግስት የቀጠለው የዒድ ገበያ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል ለሽመታ ካለመውጣቱና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የገበያው ዋጋ ያሻቀበ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው ብለዋል፡፡

የቅመማ ቅመም ገበያው የተቀዛቀዘ ነው ያሉት አቶ ሳሚር፤ የሸማቾችም ሆነ የሻጭ እንቀስቃሴ ተቀዛቅዟል። የገበያው አቅርቦትና ሽያጭ እንደ ከዚህ በፊቶቹ የበዓላት ግብይቶች አይደሉም ብለዋል፡፡

የእርድ እንስሳት፣ የስጋ፣ የወጥ እህሎች ከፋሲካ ገበያ በተመሳሳይ የግብይት ሽያጭ ቀጥሏል፡፡ ቀይ ሽንኩርት የቸርቻሮ ዋጋው ኪሎ በ48 ብር፣ ነጭ ሽንኩርት 60 ብር፣ ዝንጅብል 60 ብር እየተሸጠ ሲሆን ከፋሲካ በዓል ወዲህ የተወሰነ ጭማሪ ማሳየቱን ሸማቾችና ነጋዴዎች ተናግረዋል።

የዘይት ዋጋ በመርካቶ ገበያ ፈሳሹ ዘይት 890 እስከ 980 ብር እየተሸጠ መሆኑን ለማየት ችለናል።

ዶሮ የአበሻ ከ700 እስከ 750 እና የሸኮ ዶሮ ከ800 እስከ 850 ብር ድረስ ሲሸጥ፤ የሥጋ ግብይትም አንድ ኪሎ ከ300 እስከ 450 ብር መሸጡን ተዘዋውረን ተመልክተናል። የቅቤ ዋጋ ግብይት ከ700 እስከ 750 ብር ድረስ በመርካቶ ሲሸጥ በጢያሳ የበዓል ባዛር ገበያም ደግሞ ከ490 እስከ 550 ብር ሲሸጥ ተመልክተናል፡፡

በሾላ ገበያ የኢድ ግብይት ሲያደርጉ የነበሩት ወይዘሮ ራዉዳ ሳኒ እንደገለጹት ደግሞ፤ የዘንድሮ የኢድ ገበያ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ታይቶበታል፡፡ አንድ ኪሎ ቀይሽንኩርት 50 ብር ተሸጧል ብለዋል፡፡ የአንድ ኪሎ አይብ ዋጋ ከ 200 እስከ 250 ብር፣ የአንድ ኪሎ ቡና ዋጋ ከ340 እስከ 450 ብር እየተሸጠ እንደሆነ ገልጸው፤ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ



ፎቶ፡ ሙሳ ሙሐመድ

የሚባል የዋጋ ጭማሪ ታይቶበታል፡፡

ሌላኛው ሸማች አቶ አሕመድ ሁሴን በበኩላቸው ዶሮ በዘንድሮ የኢድ ገበያ ከ350 እስከ 800 ብር እየተሸጠ እንደሆነ ገልጸው፤ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ጭማሪ እንደታየበት ተናግረዋል፡፡

በሾላ ገበያ የቅመማቅመም እና ዶሮ ነጋዴ የሆኑት አቶ ሱልጣን አሊ በበኩላቸዉ እንደሚናገሩት፤ ዶሮ እንደ ክብደቱ መጠን ከ600 እስከ 800 ብር፣ በርበሬ በኪሎ 340 ብር፣ ሚጥሚጣ 250 ብር፣ እንቁላል የአበሻ ከ8 ብር ከ50 ሳንቲም እንዲሁም በተለምዶ የፈረንጅ እንቁላል የሚባለው ስምንት ብር፣ የምግብ ቅቤ በኪሎ 650 ብር፣ ቡና በኪሎ ከ350 እስከ 400 ብር እየሸጡ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የዘንድሮ ገበያ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ያለው መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

ርዕሰ አንቀፅ

በብሔርም ሆነ በሃይማኖት ሽፋን ኢትዮጵያን ማተራመስ አይቻልም!

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ እስልምናን ከተቀበሉ አገራት ቀዳሚዋ ስለመሆኗ የሃይማኖት አባቶችና ምሁራን የሚገልጹት እውነታ ነው፡፡ ይህንን እውነታም ነብዩ መሃመድ(ሰ.ዐ.ወ) ገልፀውታል፡፡ ሙስሊሞች መካን ይዝሙ በነበሩ ቁረሾች ችግር በገጠማቸው ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ማሳሰባቸው የሚታወስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሂጅራ የተካሄደባት አገር ስለመሆኗም የእምነቱ አባቶች ይገልጻሉ፡፡ ይህም ኢትዮጵያ የሁሉም እምነቶች ቤት ስለመሆኗ በገሃድ የሚያሳይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ እስልምናና ክርስትና ከሺህ ዓመታት በላይ በአንድ ላይ ኖረዋል፡፡ በነዚህ ዓመታትም በሌሎች ዓለማት የምንሰማቸው ግጭቶች አልተሰሙም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው በመከባበርና አንዱ የሌላውን እምነት እና ብሔር እንዲሁም ማንነቱን በማክበር መኖርን የተለማመዱ ናቸውና፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ እምነቶችም የሚታወቁት አንዱ ከሌላው ጋር ባለው የጠበቀ ግንኙነት ነው፡፡ በዚህ የተነሳ አንዱ የሌላውን ቤተእምነት በመገንባት፣ በበዓል ወቅትም በመጠራራትና አብሮ በመብላት፣ ችግሮች በሚያጋጥሙበት ወቅት በመረዳዳት፣ ከዚያም አልፎ የጋራ እሴቶችን በጋራ በመጠበቅ ነው፡፡

በአገራችን የዘመናት የአብሮነት ታሪክ ውስጥ መቻቻል፣ መተዛዘን እና መረዳዳት ያለውን ፋይዳ በውል የሚረዳው የኢትዮጵያ ሕዝብም በሰው ልጅ የዘመናት ጥረትና ድካም የዘረጋቸውን መልካም እሴቶች ኃላፊነት የማይሰማቸው አካላት በአንድ ጀንበር ሊንዱት ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ አንዴ በሃይማኖት ስም ሌላ ጊዜ በብሔር ስም ሁከትና ብጥብጥ ለማስነሳት የሚደረጉ ጥረቶች ማሳያዎች ናቸው፡፡

ሰሞኑን በጎንደር ከተማ በተለይ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮችን በማጋጨትና ይህንንም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በማስፋት በኢትዮጵያ ውስጥ የማይበርድ እሳት ለመለኮስ ሙከራ ተደርጓል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ሴራውን በውል ያልተገነዘቡ ጥቂት የተለያዩ እምነት ተከታዮች ጉዳዩን ለማራገብና አገራችንን ወደለየለት ብጥብጥ ለማስገባት የሞከሩ ሲሆን፣ አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ ግን ችግሩን በመገንዘቡ የታለመው ሴራ ሊከሽፍ ችሏል፡፡

በርግጥ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረጉ የጥፋት ተግባራት በተለያየ መልኩ ሲካሄዱ የሰነበቱ ናቸው፡፡ በተለይ ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ ኢትዮጵያን ለመበታተን የውስጥና የውጭ ኃይሎች ያልሞከሩት ጥረት የለም፡፡ ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም፡፡ በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የአማራና የኦሮሞ ሕዝብ ለማጋጨት በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡

በተጨማሪም የአማራና የትግራይ፣ የኦሮሞና የሶማሌ፣ የአፋርና ኢሳ፣ ሲዳማና ኦሮሞ ወዘተ ልዩነቶችን በማስፋት እርስ በርስ ለማጋጨት ያልተፈነቀለ ድንጋይ፣ ያልተማሰ ጉድጓድ የለም፡፡ ይሁን አንጂ እነዚህ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ላለፉት በርካታ ሺህ ዓመታት አብረው የኖሩና እርስ በርስ የተዋለዱ ጭምር በመሆናቸው መለያየት እንደማይቻል በተግባር አሳይተዋል፡፡

ባለፈው ዓርብም በአገራችን ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ የአገራችንን ገጽታ በዓለም አደባባይ ከፍ የሚያደርግ እና የእስልምና ሃይማኖትን ሰላም መሠረትነት የሚያረጋግጥ የአደባባይ የአፍጥር ሥነሥርዓት ተካሂዷል፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያን ለመበታተን ለሚፈልጉ የውስጥም ሆነ የውጭ ኃይሎች ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡

ይህ ሥነሥርዓት በአንድ በኩል የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ለሰላም ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጡና በተራ ፕሮፓጋንዳ ተነድተው ወደግጭት የማያመሩ መሆናቸውን በግልጽ ከማሳየቱም በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም የሌለ ለማስመሰል የሚጥሩ የውጭ ኃይሎች የውሸት ፕሮፓጋንዳቸውን ለዓለም አደባባይ ያሳጣ መልዕክት ያስተላለፈ ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን ጥቂት የሚባሉ በሰላማዊ ሕዝብ ውስጥ ተሰግስገው በየማኅበራዊ ሚዲያዎች ውስጥ እየተሸከረከሩ ሰላምን ለማደፍረስና አገርን ለማበጣበጥ የሚጥሩ ኃይሎች አሉ፡፡ እነዚህ ኃይሎች በተለይ በእምነት ሽፋን የተለያዩ የግጭትና የልዩነት ስብከቶችን ሲያሰራጩና ኅብረተሰቡንም ለብጥብጥ ሲጋብዙ ይታያል፡፡ ዋነኛ ዓላማቸው ደግሞ በብጥብጥ ውስጥ የራሳቸውን ጥቅም ማካበት ነው፡፡ ነገር ግን ጥፋትን በሕግ እንጂ በጥፋት ማረም ሌላ አደጋን መጋበዝ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

በመሆኑም እኛ ኢትዮጵያውያን እንዲህ ዓይነት ከፉዎችን በምንም መልኩ እንዲሰለጥኑብን የማንመች ሕዝቦች መሆናችንን ደግመን ደጋግመን ማሳየት አለብን፡፡ መላው ሙስሊም ማኅበረሰብም በኢድ ወራት ያሳየውን እርስ በርስ የመረዳዳት እና ሰላሙን የመጠበቅ የቆየ ታሪኩን በአብሮነቱ ሊያስቀጥል ይገባል፡፡

ምሁራን፣ የአገር ሽማግሌዎችና የእምነት አባቶችም ሥርዓት አልበኝነት እንዳይሰለጥን ማኅበረሰቡን በሞራልና በሥነምግባር ማነጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ክፉውን ጊዜ እንደ ዒድ ሶላት ሰብሰብ ብለን ልንጋፈጠው፣ በኅብረታችን የሚገጥሙንን ፈተናዎች እንደ ምንሻገራቸው ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያውያን ዕድል በእኛው እንጂ በሌላ በማንም እጅ እንዳልሆነ ለዓለም ማሳየት ይኖርብናል፡፡

አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ለግላችን ሳይሆን ለጋራ ህልውናችን እንድናስብ የሚያስገድደን፣ ከግል ምኞታችን በላይ ለጋራ ደኅንነታችን እንድንተጋ በእጅጉ ግድ የሚልበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ስለ ምሕረት፣ ስለ ይቅርታ እና ስለ ፍቅር እንጂ፣ ስለ ጠብና ጥላቻ ማሰብ አይቻልም፡፡ ቀጣይ ጊዜያትም ስለ አንድነት እንጂ፣ ስለ መለያየት የምንዘምርባቸው ጊዜያት ሊሆኑ አይገባም!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ሳፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpressprotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

መልካምነት መልሶ ይከፍላል

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሚያዝያ ወር ለኢትዮጵያውያን ልዩ ትርጉም አለው። ይህን ስል እንዲያው በደፈናውም አይደለም። እያገባደድነው ባለው ወር ላይ በአገራችን ሰፊውን ቁጥር የሚይዙት የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ታላላቅ ሃይማኖታዊ በዓላት (የፋሲካና የረመዳንን) በደማቅ ሥርዓት አክብረው የሚያልፉበት ስለሆነ ነው። ታዲያ በእነዚህ ክብረ በዓላት ወቅት ከምንጊዜውም በተለየ ፍቅርና መተሳሰብ፣ መተባበርና መተጋገዝ ይሰፍናል። ያለው ለሌለው ሲያካፍል አብሮ የመኖር ትርጉሙ ጣዕም እያገኘና ለትውልድ መልካም ስንቅን የሚያሻግር ድልድይ የመሆን ሥራን ይሠራል።

ብዙዎች «ኢትዮጵያዊነት መከባበርና አብሮ መብላት ማለት ነው። በደስታ፣ በኀዘንና በችግር ጊዜ መረዳዳት ነው» ይላሉ። ነገሩ አባባል ሳይሆን መሬት ወርዶ የምናየው ሃቅ ነው። ይህን ስንል ግን አባባሉን ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ እኩይ ተግባራት አይታዩም ለማለት አይደለም። ለምሳሌ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አንድነታችንን የሚያናጉ፣ አብሮ የመኖር ጥብቅ ባህላችንን ለማላላት እላይ እታች የሚሉ፣ ከኅብረት ይልቅ መለያየትን የሚሰብኩ ቡድኖች በሚፈጥሩት ቀውስ ምክንያት አያሌ ንፁሃን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፣ ተገድለዋል እንዲሁም ለረሃብና የከፋ ችግር ተጋልጠዋል። ይሄ ሁሉ ግፍና መከራን የተቀበሉት ኢትዮጵያውያን ግን ለዘመናት የገነቡት ጠንካራ ባህልና ፅኑ የኢትዮጵያዊነት መሠረት ሞራላቸው እንዳይሰበር እምነታቸው እንዳይሸረሸር አድርጓቸዋል።

የትግራይ ሕዝብ ጉያ ውስጥ ተሸሽጎ የአማራና የአፋር ክልልን መውረሩን ተከትሎ በተፈጠረ ቀውስ በርካታ ቁሳዊና ሰብአዊ ቀውሶች መከተላቸው አይዘናጋም። በወልዲያ ሕዝብ ላይ ብቻ የደረሰውን ግፍና መከራ እንደ ሰበዝ መዝዘን ለመመልከት ብንሞክር እንኳን ብዙ ብዙ በደሎችን ማንሳት እንችላለን። ይሁን እንጂ እኩይ አላማን ይዞ ሕዝቡን ለማፈናቀልና ለእርዛት ቢዳርግም የማኅበረሰቡን ቁስል እንዲሽር ግን የአንድ ሃይማኖት አባት ቀናነትና የማኅበረሰቡ እርስ በእርስ ተደጋግፎ የመኖር ባህል እንዲቀጥል ምክንያት ሆኗል። በዚያ በመከራ ጊዜ ከራሱ ፍላጎት እየቀነሰና ለተቸገረ እያካፈለ በመረዳዳት ባህሉ የችግር ጊዜውን ለመወጣት ችሏል። የወልዲያን ጉዳይ በምሳሌነት አነሳን እንጂ ችግሩ በተከሰተባቸው አካባቢዎች በሙሉ ተመሳሳይ የመደጋገፍና የመከራን ጊዜ በአንድነት እና በመተባበር ለመሻገር ተሞክሯል። አሁንም ይሄ የመተሳሰቡ ሂደት ከውጭ እስከ አገር ውስጥ ቀጥሏል።

ዛሬ ስለመረዳዳት ባህላችን ለማንሳት የወደድነው ያለምክንያት አይደለም። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ኢትዮጵያውያን አብረው የኖሩበትን ባህል ይበልጥ አጠናክረው መቀጠላቸው ስላስደሰተን ነው። ከላይ ባነሳናቸው ምክንያት ችግር ውስጥ የወደቁትን ወገኖች «ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ጌጡ» ፣ « ለወገን ደራሹ ወገን ነው» በሚል ከሚደረገው ጥረት ባሻገር በተለያየ ምክንያት አነስተኛ ገቢ ያላቸው ሁሉንም ኢትዮጵያውያን በተለይ አመት በዓላት በመጡ ቁጥር «የማዕድ ማጋራት» ቀጥሎ እናያለን። ይሄ በእጅጉ የሚበረታታ ነው።

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የፋሲካ በዓልን ባከበሩበት ባሳለፍነው ሳምንት ለተቸገሩና በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ ወገኖችን በኅብረት የመደገፍና በጋራ ተደስተው የሚያሳልፉበትን ዕድል የመፍጠር በጎ ተግባርን ሲሠሩ ተመልክተናል። ሌሎች ክርስቲያኖችም እንዲሁ በዓሉን በመረዳዳትና በማካፈል ጭምር አክብረውታል። ይሄ ኢትዮጵያዊነት ነው። ትውልዱ ከቀደሙት አባቶቹ የወረሰውና አብሮ የመኖር የጋራ እሴታችን አካል ጭምር ነው።

ቀደም ባሉት ዘመናት የአገሪቱ ዘውዳዊ ሥርዓት «ግብር ማብላት» በሚል በዓላት በመጡ ቁጥርና በተለያዩ ብሔራዊ ቀናት ማኅበረሰቡን የመርዳትና የመደገፍ ተግባር ያከናውን ነበር። ይህ የተቸገሩትን ከመርዳት ባለፈ መከባበር፣ ማካፈል መልመድ እንዲሁም አብሮ የመኖር ብልሃት አንዱ መገለጫ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በተለይ ንጉሦች መሰል ተግባር በየጊዜው ሲያከናውኑ ሕዝቡም ይህን ምሳሌ በማድረግ ካለው ድርሻውን ለጎረቤቱ የማጋራት ባህል እንዲያዳብር ያደርግ ነበር። ይሄ መልካም ድርጊትም በተደጋጋሚ ጊዜ የኢትዮጵያውያን መገለጫ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች የዓለም ክፍሎች ካሉት በተለየ መንገድ የምንታወቅበት እንዲሆን አስችሏል።

ከቅርብ አመታት ወዲህ ይህ መሰል ዘመናት የተሻገረውን ባህላችንን ወደፊት የማምጣትና ይበልጥ እንዲዳብር ለማድረግ መንግሥት እየሠራ መሆኑን ተመልክተናል። ለምሳሌ ያህል እናንሳ ብንል ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ «ማዕድ እናጋራ» በሚል አቅመ ደካማ ለሆኑና ለተቸገሩ ኢትዮጵያውያን በዓላት በመጡ ቁጥር አብረው ለማሳለፍ የሚያደርጉት ተምሳሌታዊ ሥራ አንዱ ነው።

ባሳለፍነው ሳምንት የፋሲካ በዓል ጊዜም በአንድነት ፓርክ በተካሄደ የ «እናጋራ» ርክክብ ሥነ ሥርዓት ላይ ለተቸገሩ 200 ለሚሆኑ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና አዳጊ ሕፃናት አስፈላጊ መሠረታዊ የምግብ ዓይነቶችን አጋርተዋል። በተመሳሳይ ቀን ለ230 አቅመደካሞች የምሳ ግብዣ ያደረጉ ሲሆን «የትንሳኤን በዓል ሁላችንም አቅም የሌላቸውን በመርዳት፣ ያለው ለሌለው በማካፈል መንፈስ ልናከብረው ይገባል» በማለት መልዕክት ማስተላለፋቸውን አንዘነጋውም። ለክርስትና እምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን ታላቁ የረመዳን ፆም ምክንያት በማድረግ «የአፍጥር ሥነሥርዓት» በማካሄድ ከተቸገሩት ጋር አብሮ መቆምና መረዳዳት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ለማመላከት ሞክረዋል።

መሪዎች ምሳሌ ሲሆኑ ሕዝብ ይከተላል። በጎነትን የሚሰብክ እና በተግባር የሚያሳይ ማንኛውም አካል ሌሎች እጃቸውን እንዲፈቱና ያላቸውን እንዲያጋሩ ያደርጋል። «መልካምነት መልሶ ይከፍላል» እንደሚሉት አባቶቻችን አቅመ ደካሞችን ማገዝ፣ ካለን ለሌለው ማጋራት ለምንሰጠው ሰው ብቻ ሳይሆን ለራሳችን በእጥፍ የደስታ ምንጭና ውለታ ማቆየት የምንችልበትን ዕድል የሚፈጥር ነው።

መረዳዳት ብሔር የለውም፣ መተባበር እና ችግርን በጋራ መወጣት ሃይማኖትም ሆነ ቀለምን አይመርጥም። ኢትዮጵያዊነትም በዚህ እሴት ላይ እንደተገነባ እናምናለን። ለዚያም ነው ሙስሊሙ የክርስቲያኑ በዓልን ክርስቲያኑ የሙስሊሙ በዓልን በጋራና በፍቅር ተባብሮና ተከባብሮ የሚያከብረው። ይሄ የአንድ ሰሞን ሆይ ሆይታ ሳይሆን የዕለት ተዕለት የኢትዮጵያውያን የኑሮ ዘይቤ ጭምር ነው። ጉርብትናው ጥብቅ የሆነው ኢትዮጵያዊ በደስታ፣ በችግር፣ በኀዘንና በመሳሰሉት ጊዜያት በእድር፣ በእቁብና በመዋጮ ይተጋገዛል። ሌላው ዓለም ላይ ይህን መሰል ድርጊት ማግኘት የቋጥኝ ያህል ከባድ ይመስላል።

ከመጣብን ፈተና ይልቅ ችግሩን የምናልፍበት መንገድ ፍፁም ብልሃት የተሞላበት እንደሆነ ግልፅ ነው። ለዚህ ነው ከመጋጨት ይልቅ መተባበር እንደሚያምርብን ድምፃችንን ከፍ አድርገን ለመናገር የምንወደው። ችግሮቻችንን ለመፍታት «እኛው በእኛው» የምንበቃ ለዚያም ለዘመናት ጠብቀነው የቆየነው ውድና ድንቅ የጋራ እሴቶች ያሉን ሕዝቦች መሆናችንን ማወቅ ይኖርብናል። ለዚህ ነው መልካም እሴቶቻችን እንደ ጥሩ መአዛ እንዲበዙልን ሳንታክት መሥራት የሚኖርብን።

ዜና

ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

ከተማ አስተዳደሩ በአንድ ቀን ብቻ ከ101 ሺ በላይ ለሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ አጋራ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጪውን 1443ኛውን የኢድ አልፈጥር በዓል ምክንያት በማድረግ በአንድ ቀን ብቻ ከ101 ሺ በላይ ለሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ ማጋራቱን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የኢድ አልፈጥር በዓልን ምክንያት በማድረግ ትናንት የማዕድ የማጋራት መርሃ ግብሩ ላይ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ መስጠት አያነድልም ይልቁንም ካለን ላይ ይጨምራል።

ከዚህ ቀደም የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ የኑሮ ውድነቱ ጫና የፈጠረባቸውን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውንና ምንም ገቢ የሌላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ በማድረግ ማዕድ የማጋራት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል።

በዓላት የሚፈጥሩትን ጫና ምክንያት በማድረግም ሰፋ ያለ ማዕድ የማጋራት መርሃ ግብር እየተከናወነ ነው።የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች 240 ሺ ለሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ እንደተጋራ አስታውሰዋል።

የኢድ አልፈጥርን በዓል ምክንያት በማድረግም ከአንድ መቶ አንድ ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአጠቃላይ በከተማዋ ማዕድ መጋራቱን ገልጸዋል።

መስጠት አያነድልም ያሉት ከንቲባዋ፤ « እኛ ኢትዮጵያውያን በመስጠት በመተሳሰብ፣ እርስ በርሳችን ተረዳድተን፣ አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ ተባብለን የኖርን ሕዝቦች ነን»።እርስ በእርሳችን መደጋገፋችን አላጎደለብንም ይልቁንም ጠንካራ ማኅበረሰብ ለመገንባት አጋዥ ሆኗል ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ አዳነች ገለጻ፤ በአሁኑ ጊዜ የኑሮ ውድነቱ ጫና የሚፈጥርባቸው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማችን ነዋሪዎችና ምንም ገቢ የሌላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማድረግ ተመልካች ያላቸው የመንግሥት አካል፣ የተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶችና የማኅበረሰብ ክፍሎች እንዳሉ ማሳያ ነው።የኑሮ ውድነቱ ያስከተለውን ይህን አስቸጋሪ ጊዜ በመደጋገፍ ማለፍ አለብንም ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና የበጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አስፋው ተክሌ እንደተናገሩት፤ እኔነትን በመተው እኛነትን በማስቀደም ካለን ላይ ስናካፍል ለአንድነታችን ሁሉንም ዋጋ የምንከፍል መሆናችን ማሳያ ነው።በመረዳዳትና በመደጋገፍ ይህን አስቸጋሪ ጊዜ ማሳለፍ ይገባል።የኑሮ ውድነት የተጫነው ወገናችን ማድረግ የሚቻለውን ሁሉ በትብብር መርዳት ያስፈልጋልም ብለዋል።

መደጋገፋችን ለአንድነታችንና ለአብሮነታችን ሁሉንም ዋጋ የምንከፍል ሕዝቦች መሆናችን ማሳያ ነው ያሉት አቶ አስፋው፤ መቻቻልና መደጋገፍ የሚባለውን የቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን ለዓለም ማኅበረሰብ የሰጠነው የችግሮች መፍቻ ሀብትና የማይዳሰስ ቅርሳችን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በትናንትናው ዕለት አንድ ሺ አንድ መቶ 84 ለሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች 20 ሺ 396 ኩንታል ዱቄት፣ ሰባት ሺ 134 ኩንታል ሩዝ፣ ስድስት ሺ 632 ኩንታል ማካሮኒ፣ ስድስት መቶ 63 ሺ 200 ፓስታ (በፍሬ)፣ ሦስት መቶ አራት ሺ 920 ሊትር ዘይትና ሰባት ሺ ሁለት መቶ ስድስት ካርቶን ቴምር ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። በተጨማሪም አንድ መቶ 82 በሬ፣ አንድ ሺ አንድ መቶ 76 በግ፣ 16 ሺ ሁለት መቶ አንድ ዶሮ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፤ በገንዘብ ሲተመን ከሁለት መቶ 12 ሚሊዮን ብር በላይ ነው ብለዋል።

በአጠቃላይ ከሚያዝያ አንድ ጀምሮ ባለፉት አራት ሳምንታት ለሦስት መቶ 41 ሺ 480 የኅብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፤ ማዕድ የማጋራት ሥራው ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት እንደሚቀጥልም ተገልጿል።

ከ92 ሚሊዮን ብር በላይ ግምታዊ ዋጋ ያላቸው የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በቁጥጥር ስር ዋሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ባሳለፍነው ሳምንት ከ92 ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር በላይ ግምታዊ ዋጋ ያላቸው የገቢና የወጪ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በቁጥጥር ስር መዋሉን የጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ።

በተደረገው ክትትል 90 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር የገቢና አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የወጪ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በተለያዩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ተይዘዋል፡፡

የኮንትሮባንድ ዕቃዎቹ በጉምሩክ ኮሚሽን ሠራተኞች፣ በፌዴራል ፖሊስ፣ በክልል ፖሊስ አባላትና ኅብረተሰቡ ባደረጉት የጋራ ጥረት በፍተሻ፣ በበረራና በጥቆማ የተያዙ ናቸው። የኮንትሮባንድ ዕቃዎቹን ሲያዘዋውሩ የተገኙ አስር ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

በቁጥጥር ስር ከዋሉት የኮንትሮባንድ ዕቃዎች መካከል አልባሳት፣ ነዳጅ፣ የቁም እንስሳት፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ቡና፣ መድኃኒት፣ ተሽከርካሪዎች፣ የመዋቢያ ዕቃዎች የጦር መሣሪያዎች፣ አደንዛዥ እጾችና የተለያዩ አገር ገንዘቦች ይገኙበታል፡፡

በዚህ የሕግ ማስከበር ሥራ ላይ ለተሳተፉ የኮሚሽኑ ሠራተኞች፣ የክልልና የፌዴራል ፖሊስ አባላት እንዲሁም ለመላው ሕዝብ ኮሚሽኑ አመስግኗል።

ሁሉም ባላድርሻ አካላትና ኅብረተሰቡ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ የጉምሩክ ኮሚሽን ጥሪ አቅርቧል።

«ኃላፊነት የሚሰማው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አንድነታችንን ለማጠልሸት እየሠሩ ነው። ሆኖም ኢትዮጵያን በጥላቻ ታውሮ ማሸነፍ እንደማይቻል ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በፍቅር ተነሳስቶ መስዋዕትነት ከፍሎ ኢትዮጵያን ማጽናት ነው የሚቻለው ብለዋል።

ፈታናዎች እና የሚያደናቅፉን ቢበዙም በየቀኑ እየበረታን እንሄዳለን፡፡ የኢትዮጵያ የመጀመሪያውም ሆነ የመጨረሻው ምሰሶ የአገር መከላከያ እንደሆነም አስታውቀዋል።

በጉብኝቱ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት እና የአገር መከላከያ ሠራዊት አመራሮች ተገኝተዋል።

መንግሥት ለሠራተኞች ዝቅተኛ የደመወዝ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የጀመርነው ጉዞ ይበልጥ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ሚኒስትሯ፤ አንዳንድ የተጀመሩ ሥራዎች ግን ምክንያታዊ ጊዜን የሚፈልጉ መሆናቸው ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት ሲሉ ገልፀዋል።

በሠራተኛው በኩል ክህሎትን ያለማቋረጥ ማሻሻል እና የሠራተኛውን የመደራጀት መብት ማስከበር የመደራደር አቅሙን ስለሚጨምርለት እዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ብለዋል።

የሠራተኛው መደራጀት ለተጀመረው የዴሞክራሲ ትግል እና የልማት ጉዞ ትልቅ ትርጉም እንዳለው የገለፁት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ ለአሠሪ ተቋማት የሠራተኛው መደራጀት አቅምና ሥንቅ እንጂ ሥጋት ሊሆን አይገባም ብለዋል፡፡

ሚኒስትሯ እንዳሉት፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት አገራዊ ለውጡን መሠረት ባደረገ አኳኋን ሕጎችንና ፖሊሲዎችን የመፈተሽ ሥራዎች ተሠርተዋል። የሠራተኛውን ድምፅ የሚወክሉ አደረጃጀቶችን በማሳተፍ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች ላይ በርካታ ጥረቶች እየተደረገ ይገኛል።ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ ያሉ ተደማሪ ውጤቶች ያሉ ቢሆንም በቂና አርኪ አይደሉም፡፡

የኢትዮጵያ ሠራተኛና ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) ፕሬዚዳንት አቶ ካሳሁን ፎሎ በበኩላቸው ሠራተኛው በርካታ ያልተመለሱ ጥያቄዎች እንዳሉት ተናግረዋል።የኢትዮጵያ ሠራተኞች የሰላም፣ የኑሮ መሻሻል እና የሥራ ላይ ደህንነት ጥያቄዎች በአስቸኳይ ሊመለሱ ይገባል ብለዋል፡፡

ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል አለመወሰን፤ የኑሮ ውድነቱ ሠራተኛው ላይ ያስከተለው ጫና፤ በነፃነት የመደራጀት እና የመደራደር መብት እና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎች በሠራተኛው ላይ የተጋረጡ አንገብጋቢ ችግሮች መሆናቸው መታወቅ አለበት።የባለድርሻ አካላት ትብብር እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት በአስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጠን በኢትዮጵያ ሠራተኞች ሥም አጥብቀን እንጠይቃለን ብለዋል፡፡

ትናንት በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ የተከበረው የዓለም ላብ አደሮች ቀን (ሜይዴይ) ዛሬ ሚያዝያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም በዓለም ለ133ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ለ47ኛ ጊዜ ተከብሮ ይውላል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

ነፃ ሃሳብ

በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቀምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

ያልተሄደበት መንገድ፣ የሸማች ጋዜጠኝነት...!?

እንደ ማሳያ፡- ሰሞኑን የትንሳኤን በዓል ታክኮ ቅቤ ከ800 እስከ 1000 ብር ተሸጧል። በመርካቶ፣ በሾላና በሌሎች ገበያዎች ያሉ ነጋዴዎች ለምን እንደጨመረ በጋዜጠኞች ሲጠየቁ ከመጣበት ቦታ ስለጨመረ ነው የሚል የተለመደና ተዓማኒነት የሌለው መልስ ይሰጣሉ። ጋዜጠኛውም ከየት ነው የመጣው? በስንት ተረከባችሁት? ብሎ መጠየቅ ሲገባው እንደ ገደል ማሚቶ የተነገረውን መልሶ ያስተጋባል። የሸኖ ለጋ፣ የወለጋ፣ የጎጃም ቅቤ ከሆነ አዲስ አበባ እየተሸጠበት ያለውን ዋጋ መነሻ በማድረግ ከአካባቢው የገበያ ዋጋ ጋር በማመሳከር የመጣበትን ዋጋ በማጋለጥ ስግብግብ ነጋዴዎችን ማሳጣትና ማስነወር ይችላል። ጋዜጠኛው ግን ይህን አላደረገም። ለዚህ ነው ዘገባው የቢዝነስም የኢኮኖሚም የማይሆነው ። ቁንጽልና ሚዛናዊ ስላልሆነ።

የሚገርመውና የሚያሳዝነው ከእነዚህ አካባቢዎች የመጣ ንጹሕ ቅቤ በምኖርበት አካባቢ ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ በሚያስረክቡ ነጋዴዎች በ500 ብር ሒሳብ ነው የተሸጠው። እንግዲህ እነዚህ ነጋዴዎች በትንሹ ከኪሎ 100 ብር ቢያተርፉ የመጣበት ዋጋ 400 ብርና ከዚያ በታች ነው ማለት ነው። የመርካቶና የሾላ ቅቤ ነጋዴዎች ደግሞ ቋሚ አቅራቢዎች ስላሏቸው ከዚህ ባነሰ ዋጋ እንደሚረከቡት መገመት ይቻላል። ታዲያ ለምን ከ800 እስከ 1000 ብር ይሸጣሉ ከተባለ መልሱ ስግብግብነትና አልጠግብ ባይነት ነው። ይህ የሆነው ደግሞ እነሱ እንደሚዋሹትና እንደሚያታልሉት የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ተፈጥሮ አይደለም። መጀመሪያ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን፤ አሁን ደግሞ የዩክሬንና የራሽያን ጦርነት ተከትሎ የተከሰተው የዋጋ ጭማሪ እንዳለ ሆኖ፤ ዘይትን ጨምሮ በሌሎች መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ የሚታየው የዋጋ ጭማሪም ከዚህ የሚመነጭ ነው።

ሌላው ገበያውን እያናጋ ያለው ያልተገባ ትንበያ፣ ሟርትና ስጋት ነው። የገንዘብ ሚኒስቴር ዴኤታው በዚያ ሰሞን በቅንነት በአንድ ቴሌቪዥን ቀርበው በዓለማችን የስንዴና የምግብ ዘይት ከፍተኛ አምራችና አቅራቢ የሆኑት ራሽያና ዩክሬን ወደ ጦርነት መግባታቸው በአቅርቦትም ሆነ በዋጋ ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል ባሉ ማግስት፤ ዘይት ወደ 1000 ብር ከመተኮሱ በላይ ወዲያው ከገበያ እንዲጠፋ ተደረገ። ስንዴም እንደዚሁ። እንግዲህ ይታያችሁ ጦርነቱ ከመቀስቀሱ ከወራት በፊት የገባ የምግብ ዘይት ዋጋ ነው በዛ ደረጃ በአንድ ጀምበር የተተኮሰው። ስለዚህ ትንፍሽ ያላለው ሚዲያ ሰሞኑን ደግሞ በአናቱ ኢንዶኔዥያ የፓልም ዘይት ለውጭ ገበያ እንዳይቀርብ አገደች በማለት የፓልም ዘይት ዋጋን ለሌላ ጭማሪ እያመቻቸው ነው።

ሚዲያውም ሆነ የመንግሥት ባለስልጣናት እንዲህ ካለ የገበያ ትንበያ/ማርኬት ስፔኩሌሽን/መታቀብ አላቸው። እያንዳንዷ መረጃ ከገበያ አንጻር እንደምትተረጎም ልብ ማለት ግድ ይላል። ደላላውና አሻጥረኛ ነጋዴው የሚነዛው የገበያ ሽብር መች አነሰን። ይህ የቢዝነስ ዘገባዎቻችን ልምሻ ሌላው ማሳያ ነው ። ለዚህ ነው ከዚህ ጥንቃቄና ማስተዋል ከጎደለው ግልብ ዘገባ ወጥቶ የሸማች ጋዜጠኝነትን መተግበር ያሻል የምለው።

በተፈጥሮዬ ጨለምተኛ ባልሆንም ዛሬ በሃገራችን እየተስተዋለ ያለው እጅግ አንገብጋቢና አስፈሪ እየሆነ የመጣውን የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት በተቀናጀ ርብርብ ካልተገታ ውሎ አድሮ የህልውና፣ የደህንነት፣ የሰላምና የጸጥታ ችግር እንዳይሆን ያሰጋኛል። ያስፈራኛል። የኑሮ ውድነቱ ከማስበውና ከምገምተው በላይ ስር የሰደደና ውስብስብ ሆኖ ይሰማኛል። በመሆኑም በቀላሉና በአጭር ጊዜ የሚስተካከል አይደለም። ከቀረጥ ነጻ መሠረታዊ ሸቀጦችን በማስገባት፣ በሰንበት ገበያና በፍራንኮ ቫሉታ የሚቀረፍ አይደለም። መፍትሔው በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራ የተቀናጀና ዘርፈ ብዙ ምላሽና ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ይጠይቃል። በተለይ የገዥው ፓርቲ ብልጽግና ወጥ የሆነ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት እጅግ ወሳኝ ነው። ይሄን ለማድረግ ግን የዋጋ ግሽበቱን ዳራና ውስብስብነት በልኩ መረዳት ያስፈልጋል።

ዛሬ የምንገኝበት የኑሮ ውድነት የዋጋ ግሽበት ቢያንስ ላለፉት 50 ዓመታት ሲድህ የመጣ ነው። በሕወሓት/ኢሕአዴግ ደግሞ በተለይ 1997 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ ሶምሶማውን ተያያዘው። ካለፉት ሰባት ዓመታት ወዲህ ደግሞ እንደ ፈጣን ሯጭ መፈትለክ ጀመረ። 390 ብር የነበር ዘይት ከእጥፍ በላይ ጋሽቦና ተተኩሶ 1000 ብር ገባ። በሌሎች ተመሳሳይ መሠረታዊ ሸቀጦች ላይም ግሽበቱ ተመሳሳይ ሽምጥ ጋለበ ። ደረጃው ይለያይ እንጂ በደርግም በኢሕአዴግም ኢኮኖሚው መዋቅራዊና ተቋማዊ ችግር ነበረበት ። ድንገት ተነስቶ ባለፉት አራት ዓመታት የተከሰተ ከመሠለን ተሳስተናል ። ለዚህ ነው የዚህን የኑሮ ውድነት ዳራና ውስብስብ ችግሮቹን በማዕቀፍ በጥልቅ መመልከት የግድ የሚለው። ግልብ ዕይታ ለቁንጽልና ግልብ መፍትሔ ይዳርጋል። ይህ አካሄድ እሳት ማጥፋት እንጂ ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም ። ሕዝብም ሆነ ሸማቹ የተሟላ ግንዘቤ እንዳይኖረው ያደርጋል። መንግሥትም የተሟላ ስዕል እንዳያይ ያደርገዋል።

ብዙኃን መገናኛዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና እንደ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበራትና የዘርፍና የንግድ ምክር ቤት ያሉ ተቋማት እየመጣ ያለውን ቀውስ ቀድመው ተንብየው የማንቂያ ደወሉን ሊነኩ ይገባ ነበር ። የመፍትሔ ፈለገ ካርታ ሊነድፉ ይገባም ነበር ። በተለይ አንጋፋው የአአዩ በጥናትና በምርምር ታግዞ እየመጣ ስላለው ችግር መንግሥትን ደጋግሞ ሊወተውትና የመውጫ የሚያመለክቱ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችንና የፖሊሲ ሀሳቦችን ሊያመላክት ይገባ ነበር ። ዩኒቨርሲቲው ግን በሚያሳፍር ሁኔታ ባለፈው ሰሞን እንደተቀረው ሸማች በኑሮ ውድነቱ የተነሳ ለተማሪዎች ምገባ የሚውሉ መሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋ አልቀመስ ማለቱን በመግለጽ ሙሾ ሲያወርድ መስማት ያሳፍራል። የመፍትሔው አካል መሆን ሲገባው የችግሩ አካል መሆንን መረጠ።

በነጻ ገበያ ስም ስድ የተለቀቀው የግብይት ሒደቱና ስንሰለቱ ሸማቹን ለከፋ ምሬትና እሮሮ እየዳረገውና ሕይወቱን እያመሰቃቀለው ነው። ሃገሪቱ ለቀደሙት 20 እና ከዚያ በላይ በነበሩት ዓመታት ትከተለው በነበረ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እየተባባሰ የመጣው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት፤ ከለውጡ በፊት ለተከታታይ ሶስት ዓመታት ከለውጡ በኋላ ደግሞ ለአራት ዓመታት የቀጠለው ግጭትና አለመረጋጋት፤ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የፈጠረው የሎጂስቲክስና የምርት መስተጓጎል ፤ አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ በፈጸመው ታሪክም ሆነ ትውልድ በማይረሳው ክህደትና ጭፍጨፋ ሃገሪቱ ተገዳ ወደ ጦርነት መግባቷ ፤ በግብይት ስንሰለቱና ሒደቱ የሚስተዋለውን አጉራ ዘለልነት ሥርዓት ለማስያዝ በገዢው ፓርቲ ብልጽግና ወጥ የሆነ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት አለመኖሩ፤ አንዳንድ አመራሮችም ከሕገ ወጥ ነጋዴዎችና ደላላዎች ጋር የጥቅም ትስስር ፈጥረው መገኘታቸው ችግሩን ከቀን ወደ ቀን እያባባሰውና ወደማይገመትና ማይታወቅ አደገኛ ስፍራ እየወሰደው ይገኛል።

ሆኖም ገዥው ፓርቲም ሆነ ተፎካካሪዎች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ዩኒቨርሲቲዎች የምንገኝበትን ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ወጥ በሆነ አግባብ እንዲረዱት ሚዲያው ከግልብ የቢዝነስና የኢኮኖሚክስ ዘገባ ወጥቶ በምርመራ ጋዜጠኝነት የታሸ የሸማች ጋዜጠኝነትን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። በነገራችን ላይ የሸማች ጋዜጠኝነት ለሕዝቡ የተተነተኑ፣ የተተረጎሙና የተመረመሩ የገበያ መረጃዎችን ለሸማቹ ወይም ለሕዝቡ የማድረስ የጋዜጠኝነት ዘውግ ነው። ወቅታዊ መረጃዎችን ከስር ከስር እያነፈነፈ ወዲያው ወዲያው በማቅረብ ለሸማቹ የሸመታ ውሳኔ በአዎንታ በግብዓትነት የሚያገለግል የቢዝነስና የኢኮኖሚክስ አይነት ነው። የገበያውን አካሄድ ፤ የሸቀጦችን ዋጋ ፤ ሸማቹ አንድን መሠረታዊ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት ቢገበይ የሚያገኘውን ጥቅም ወይም ጉዳት ቁልጭና ፍንትው አድርጎ የማሳየት ጋዜጠኝነት ነው ። አሁን በኢቢሲ ፣ በፋና ፣ በዋልታና በሌሎች ብዙኃን መገናኛዎች እየታዘብነው ያለው ዘገባ ግን አይደለም ለሸማች ጋዜጠኝነት ለቢዝነስና ኢኮኖሚክስና አቅመ ዘገባነት ያልደረሰ ግልብና መናኛ ቁንጽል መረጃ እንጂ ለሸማቹም ሆነ ለመንግሥት ውሳኔ መነሻ ሊሆን የሚችል አይደለም ። በተለይ መንግሥታዊ ብዙኃን መገናኛዎች ለስብሰባ አዳራሽና ለሁነት ዘገባ ከሚሰጡት ትኩረትና ሰፊ ሽፋን ቀነስ አድርገው ለሸማች ጋዜጠኝነት ልዩ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል ።

እንኳን እንደ ትንሳኤና ዒድ ያሉ ታላላቅ በዓላት መጥተው ይቅርና በአዘቦትና በሰርክም ሁል ጊዜም በጥፍራቸው ቆመው ዋጋ ለመጨመር የጥፍ ስንጥቅ ለመግፈፍ (በዚህ መጠን የሚጋበስ ትርፍ ሳይሆን ሸማቹን በቁሙ መግፈፍ ነው ብል ስለማምን ነው፤ መግፈፍ ያልሁት) ሰበብ አስባብ የሚጠባበቁ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት እና ደላሎች አሉ። 100፣ 200፣ 300፣ 400፣ 500፣ ...1000 በመቶ ካላተረፉ የነገዱ የማይመስላቸው ስግብግብ ነጋዴዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ነው ። ሰሞኑን እያስተዋልን ያለው መረን የለቀቀውን ስግብግብነት ነው ። ጨዋና ለወገናቸው የሚራሩ ጥቂት በጣም ጥቂት ነጋዴዎች መኖራቸው እንዳለ ሆኖ። ይሄን አጉራ ዘለልና ሥርዓት አልባ የግብይት ሥርዓት እየተከታተለ በማጋለጥ ረገድ የሸማች ጋዜጠኝነት በምንም የማይተካ ሚና አለው።

በአሸባሪዎቹ ሕወሓትና ሸኔ በተከፈተው ጦርነት፤ የራሽያንና የዩክሬን ጦርነትን፤ የውጭ ምንዛሪ ዕጥረትን፤ መንግሥት መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ያደርገው የነበረ ድጎማ በመሐል በማንሳቱ፤ የአቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠን በመኖሩ ፤ በእንቅርት ላይ እንዲሉ አጉራ ዘለል የግብይት ሥርዓት ፣ ሙስናና ደላላ ተጨምሮ ሸማቹን በኑሮ ውድነትና በዋጋ ግሽበት ጉማሬ እየገረፈው ነው። ለድምጽ አልባ ረሀብ እየዳረገው ነው ። ድሮም ከእጅ ወደ አፍ የነበረው ኑሮው አልቀመስ እያለውና እያማረረው ነው ። ሆኖም ብዙኃን መገናኛዎቹ በልኩና በደርዙ እየዘገቡት አይደለም ። የዘገባዎቻቸው መሪ ዜና ሊሆን ሲገባ መጨረሻ ላይ ለዛውም በጥድፊያና በግልብ እየታለፈ ነው ። የገበያ ዘገባዎቻቸውም ባዶ የቁጥር ኳኳታ እንጂ በቅጡ የተተረጎሙ አይደሉም።

ይሄ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ሀይ ባይ የሚያገኘው መቼ ነው!? እንዳሻቸው ዋጋ የሚቆልሉ ስግብግብ ነጋዴዎችስ መቼ ይሆን በሕጋዊው የገበያ ሥርዓት የሚመሩት !? መንግሥትስ በነጻ ገበያ ስም ስድ የለቀቀውን ገበያ በዋጋ ጣራና የትርፍ ህዳግ ልጓም የሚበጅለት መቼ ነው!? ሁሉንም ገበያ እንዳሻው ቁጭ ብድግ የሚያደርገው ደላላስ መቼ ይሆን ከሻጩም ከሸማቹም ጀርባ የሚወርደው!? ለመሆኑ የትላንቱም የዛሬውም ንግድና ኢንዱስትሪም ሆነ የዛሬው የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ምን ሠራ!? ምን እየሠራ ነው!? እነዚህ ጥያቄዎች ለዘመናት ተነስተዋል ። መልሳቸውን የበላ ጅብ አልጮኸም እንጂ ። ከታች እስከ ላይ ያለው አመራርስ የሃገር ህልውና አደጋ ለመሆን ጫፍ የደረሰውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ለመከላከል ወጥ የሆነ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት አለው ወይ!? በግብይት ሰንሰለቱና ሥርዓቱ የሚስተዋለውን ሥርዓት አልበኝነት አደብ ለማስገዛትና የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እውነት አመራሩ ቁርጠኝነት አለው!? መንግሥት በሚያወራው ልክ እየሠራ ነው ወይ!? መልሱ አይደለም ነው።

ምክንያቱ ችግሩ እየተባባሰና ገበያውም ሆነ ኢኮኖሚው ከእጁ እየወጣ ነው። ሥርዓት የማያሲዘውን ገበያና ኢኮኖሚ እየመራሁት ነው ማለት ስለማይችል። ሆኖም ብዙኃን መገናኛዎች እነዚህን ክፍተቶችን ለመንግሥት በቅጡ እያሳዩት አለመሆኑ ይበልጥ ያሳስባል። ያሰጋል ። የራሽያና የዩክሬን ጦርነት ፣ ኮቪድ 19 ፣ በሃገሪቱ የተቀሰቀሰው ጦርነት፣ እዚህም እዚያም የሚስተዋለው ግጭት ፣ የጸጥታና የደህንነት ችግሮች ፣ የምርት እጥረት ፣ ወዘተረፈ አሁን ስልጣን ላይ ያለው መንግሥት የፈጠራቸው ችግሮች አይደሉም ። ጦርነቱም ተገዶ የገባበት ነው ፤ በሶስት ሳምንት የተቀዳጀውን ድል ማስጠበቅ ፣ ማዝለቅና ማጽናት ላይ የነበረበት ክፍተት ለሁለተኛው ጦርነት ቢዳርገውም። ላለፉት ሰባት ዓመታት በተለይ ላለፉት አራት ዓመታት በመላው ሃገሪቱ የተቀሰቀሱ ጭፍጨፋዎች ፣ ብጥብጦች ፣ ቀውሶች ፣ ግጭቶች ፣ መፈናቀሎች ፣ ወዘተረፈ ለቀደሙት 27 ዓመታት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆኖ ሲቀነቀንና ሲነዛ የኖረው ጥላቻ ፣ ልዩነት ፣ ቂም ፣ በቀል ፣ ዘረኝነትና ሐሰተኛ ትርክት የወለዳቸው መሆኑን ብዙኃን መገናኛዎች አብራርቶና አፍታቶ ለአድማጭና ለተመልካች ማድረስ ላይ ውስንነት አለባቸው ።

ሆኖም አሁን ስልጣን ላይ ያለው መንግሥት የዋጋ ግሽበቱንና ተከትሎ የመጣውን አደገኛ የኑሮ ውድነት በአቅሙ ማን ደግሞ ማድረግ የሚገባውን አበክሮ አልሠራም። አጉራ ዘለል የሆነውን የግብይት ሒደት በሕግ፣ በአሠራርና በአደረጃጀት መግራት እየቻለ ከቀውሱ አሳሳቢነት አንጻር አለመንቀሳቀሱን ፤ በግብይት ሰንሰለቱ ከጉልት እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰጉ ደላላዎችን ሥርዓት ለማስያዝ አለመንቀሳቀሱ ፤ ስግብግብ አከፋፋዮችና ነጋዴዎች “ነጻ ገበያው”ን መሠረታዊ ሸቀጦችን በመደበቅና ዋጋቸውን በአድማ በመወሰን ሰው ሰራሽ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት በመፍጠር ሽባ ሲያደርጉት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በልኩ አለመንቀሳቀሱን ብዙኃን መገናኛዎች በአግባቡ አላሳዩም ።

የንግዱ ማኅበረሰብ ራሱ ያላከበረውን “ነጻ ገበያ” መንግስት “ነጻ ገበያ ነው” እያለ 120 ሚሊዮን ሸማች ሲታገት ባልሰማና ባላየ ማለፉ አሁን ለምንገኝበት ቀውስ ዳርጎናል ። ስለሆነም በግብይት ሒደቱ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ለነገ የሚተው ጉዳይ ስላልሆነ ፈጥኖ መንቀሳቀስ አለበት። የንግዱ ማኅበረሰብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እየጣሰው ያለውን “ነጻ ገበያ” እስኪያከብረው ድረስ ሌላው ይቅርና ከመርካቶ አምጥቶ እጥፍ ስንጥቅና ከዚያ በላይ ካላተረፈ የነገደ ስለማይመስለው በተለይ በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ የዋጋ ተመንና የትርፍ ሕዳግ ሊቀመጥ ይገባል ። ገበያው ላይ ኮሽ ባለ ቁጥር የኪራይ ዋጋ የሚቆልለው የንግድም ሆነ የመኖሪያ ቤት አከራይ እስኪሰክን ድረስ የኪራይ ተመን ተግባራዊ መደረግ አለበት።

ዓለማቀፍ የፋይናንስ ጉምቱው (Guru) አቶ ኤርሚያስ አመልጋ በዚያ ሰሞን ከ”Arts tv በነገራችን ላይ ...!?” በነበራቸው ቆይታ መንግሥት የዋጋ ግሽበቱንና እሱን ተከትሎ እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት በማያዳግም ሁኔታ ለመፍታት የውጭ ምንዛሪን እጥረቱን መቅረፍ አለበት ። ይሄን የውጭ ምንዛሪ ችግር ለመቅረፍ ደግሞ ይችላል ። የሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት የቱንም ያህል ከፍተኛ ቢሆንም ከአራት ቢሊዮን አይበልጥም፤ ይሄን የውጭ ምንዛሪ መንግሥት አቅርቦ እጥረቱን ማቃለል ቢቻል የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሽበቱን በዘላቂነት መቅረፍ ይቻላል። ግብጽን ገጥሟት የነበረውን ተመሳሳይ ችግር በማያዳግም ሁኔታ መቅረፍ የቻለችው የውጭ ምንዛሪ እጥረቷን በመፍታት ነው ብለዋል ። የሚገርመው አንድም የመንግሥት ብዙኃን መገናኛ ይሄን ሀሳባቸውን አጀንዳ አድርጎ የሞገተ ፣ ያስተቸና ያስሄሰ አለመኖሩ ነው ።

ከዚህ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ቀለበት ሰብሮ ለመውጣት ከፍ ብሎ ለማሳየት እንደምከርሁት ያልተሄደበትን መንገድ መያያዝ ግድ ይላል ። ከዘመቻና እሳት ከማጥፋት አሠራር ወጥቶ ስትራቴጂካዊ ዕይታን መከተል ያሻል ። ሃገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፣ የአረንጓዴ አሻራ፣ የበጋ ስንዴ ፣ የግብርና ሜካናይዜሽን ፣ የመስኖ ልማት ፣ ኩታ ገጠም ግብርና ፣ ወዘተረፈ ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ የተወሰዱ እሰይ የሚያስብሉ ስትራቴጂካዊ ዕይታዎች ናቸው። ከዚህ ጎን ለጎን የግብይት ሒደቱን አንቀው የያዙ ማነቆዎች ካልተፈቱ ፤ ደላላው ከግብይት ሒደቱ ካልወጣ ፤ በነጻ ገበያ ስም ምርት የሚደብቁ ፣ ዋጋ በአድማ የሚወስኑ ስግብግብ ነጋዴዎች ላይ አስተማሪ እርምጃ ካልተወሰደ ፤ በመንግሥት መዋቅር የተንሰራፋው ብልሹ አሰራርና ሙስና ካልተወገደ ምርት የቱንም ያህል ቢጨምር ከዚህ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ቀለበት ሰብሮ መውጣት አይቻልም። የሸማች ጋዜጠኝነት ይሄን የትኩረትና የአይታ ሚዛናዊነት በማስጠበቅ ረገድ ብዙ ይጠበቅበታል ።

ማህበራዊ

የሕይወት ገጽታ

ዝግባው አቶ ብርሄ ጋሹ

አሥመረት ብሥራት

"ቁመትሽ ሎጋ ነው ሰንደቅ ያሰቅላል ..." ከሚለው ዘመን ተሻጋሪ ጥሩም ዜማ አንሰቶ "ጠይም ዘለግ ያለ ..." እስከሚለው ድረስ ቁመት የውበት መገለጫ ሆኖ በሃገራችን ዘፈኖች መካከል ብቅ ብቅ ሲል ይደመጣል። መቼም ረዘም ያለው የመወደዱን ያህል ቁመት በዛ ሲል ደግሞ "ብቅል አውራጅ"፤ "ዛፉ" እና ሌሎች ቅፅል ስሞች እየተሰጡት ሲጠራም እንሰማለን። ስዛሬ የሕይወት እንግዳችን የሆኑት አቶ ብርሄ ጋሹም ቁመታቸው ከመርዘሙም በላይ እንደ ሰማይ ስባሪ የሚታዩ ቅፅል ስማቸውም "ዛፉ" እንደሆነ ነግረውናል።

ደማቅ ፈገግታ ፈታቸው ላይ የሚነበበው እኚህ ዘንካታ ሰው በፍጹም ቤተሰባዊ ስሜት ስቃስ መጠይቅ ወደ ተቋማችን በመጡበት ወቅት ስከበባቸው ሰው ሁሉ ሰላምታ ይሰጣሉ። በግርምት ከሚመለከታቸው ሰው ባሻገር አብሬ ፎቶ ልነሳ ላለው ሰው በሙሉ ፈቃደኝነት እየቆሙ በመነሳት ወደ ውስጥ ዘልቀናል። ትህትና አክብሮት በሚታይበት ፌት ተወልደው ባደጉበት በጎጃም አካባቢ የንግግር ዘዴ እንዲህ ተጨዋውተናል፤ መልካም ንባብ።

አቶ ብርሄ ጋሹ ትውልድና እድገታቸው በጎጃም፣ አዊ ብሔረሰብ ዞን፣ ፋግታ ለኮማ ወረዳ፣ ድማማ አንገረፍ ቀበሌ፤ አንገረፍ ጊዮርጊስ በምትባል ልዩ አካባቢ ውስጥ ነው። ልጅ ሆነው እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የገጠር ሕጻን በተለመደ የአስተዳደግ ዘዴ ማደጋቸውን የሚናገሩት ልጅ እያሉ ከጓደኞቻቸው የተለየ ቁመት እንዳልነበራቸው ያስታውሳሉ። አቶ ብርሄ ቁመታቸው እየተመዘዘ መሆኑን ያወቁት እድሜያቸው ወደ ጉርምስናው እየተጠጋ ባለበት ጊዜ እንደነበር አይረሱም።

"ልክ ቁመቴ እየተመዘዘ ሲሄድ ማን በስሜ ይጥራኝ። ሁሉም ሰው ብርሄ የሚለውን ስሜን ረስቶ ዛፉ፣ ዝግባው . . . ሆነ መጠሪያዬ። እኔም ብሆን ካለሁበት አካባቢ ሰው የተለየሁ መሆኔን ሳስበው ከገበያውም ከአካባቢው ሰው ልዩ መሆኔ ይሰማኝ ጀመር።" የሚሉት አቶ ብርሄ "ሰው በታች እያለ እኔ በፈረስ ላይ ሆኜ እንደምሄድ ነው የምታየው" ይላሉ።

"አቶ ብርሄ መች ተወለዱ?" ስንል ላቀረብንላቸው ጥያቄ "እኔ ማንበብም መፃፍም አላውቅም፤ የትውልድ ዘመኔ ይህ ነው ብዬ ባልናገርም አሁን እድሜዬ 38 ደርሷል።" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። አቶ ብርሄ አሁን በመገናኛ ብዙኃን ከታዩ በኋላ ለጋስ ኢትዮጵያውያን በርካታ ጫማዎችን ሳያበረክቱላቸው በፊት በሕይወታቸው አንድም ቀን ጫማ ተጫምተው አያውቁም ነበር።

ቁመታቸው 2 ነጥብ 50 ሜትር የሆነው አቶ ብርሄ ምስላቸው ሕዝብ ዘንድ የደረሰበትን አጋጣሚ እንዲህ ይተርካሉ። "በአካባቢያችን በበጋ መስኖ እርሻ የተዘራን ስንዴ ለመጎብኘት የአካባቢው የሥራ ኃላፊዎች ወደ ወረዳው በመጡበት ወቅት አብራ የመጣች ጋዜጠኛ ቁመታቸውን በመመልከት በጣም ተገርማ አንድ ፎቶግራፍ በማንሳት ካስተዋወቀች በኋላ በርካታ የመገናኛ ብዙኃን ወደ'ነ አቶ ብርሄ ቀዬ መጉረፍ መጀመራቸውን ይናገራሉ። በወቅቱ የልማት ሥራውን ለመጎብኘት የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ዶክተር ይልቃል ወደ አንገረፍ አቅንተውም ነበር። ብዙ እንግዶችም አብረዋቸው ነበሩ። አቶ ብርሄም ተጠርተው ርዕሰ መስተዳደሩን በአካል ከማግኘታቸውም ባሻገር አብረውም ፎቶ መነሳታቸውን ያስረዳሉ።

"ቁመትዎ አስቸጋሪ ሆነብዎት ያውቃል?" በማለት ላነሳንላቸው ምላሽ የሰጡት አቶ በርሄ "ረጅም መሆኔን እግዜር እንዴ ከሰጠኝ ምን አደርጋለሁ ብዬ ብኖርም እየዋለ እያደረ ደግሞ ችግር አመጣብኝ። ሥራ መሥራት አልቻልኩም። ማረስ ፈተና ሆኖብኛል። ለበሬዎቹ የሚስማማው ሞፈር እና ቀንበር ሳዘጋጅ እኔን አስጎንብሶ ወገቤን ሊሰብረው ይደርሳል። ለምን

ፎቶ፡ በላይ ንጉሤ

በቁመቴ የሚስማማ አላደርግም ሲል ደግሞ በሮቹ አልተመቻቸውም፤ ለገሙ። አልንቀሳቀስ አሉ። ስለዚህ አርሶ መብላት ለኔ ፈተና ነው።" ይላሉ።

በቁመታቸው የተነሳ የሚገጥማቸው ፈተናው በዚህ ብቻ አያበቃም። የሚበቃቸውን ልብስ ስለማያገኙ በልካቸው ለማሰፋት ለሁለት ሰው በሚበቃ ዋጋ ጨርቅ ይገዛሉ። "ልብስማ ያው ወጪ ይጠይቀኛል እንጂ ሁለት ሰው የሚሉበሰውን ባለሙያዎች ይሰሩልኛል። ልብስ ሳሰፋ እንደ ጨርቁ ሁኔታ ለሁለቱ ሰው የሚሆነው ለእኔ ይበቃኛል። ለአንድ ጊዜ 1500 ብር እንደዛ አካባቢ እከፍላለሁ። የሁለት ሰው ሂሳብ ነው የምከፍለው" ሲሉ ያስረዳሉ።

ወደ መገናኛ ብዙሃን ብቅ ካሉ በኋላ በለጋሶች እንዲህ ጫማ በጫማ ሳይሆኑ በፊት እግራቸውም ጫማ አይቶ አለማወቁን እንዲያውም የጫማ ቁጥራቸውንም እንደማያውቁት ይናገራሉ። "እሰካሁን ጫማ የማልለብስብት ምክንያት እግሬም እንደ ቁመቴ አብሮ ስላደገ ገበያ ላይ ያለው ጫማ ስለማይበቃኝ ነበር" የሚሉት አቶ በርሄ "አሁንማ እድሜ ለሃገሬ ሰው አንዱ ቀዩን፤ አንዱ ጥቁሩን ባይነት ባይነት እያመጣልኝ ባለ እልፍ ጫማ ሆኛለሁ" ይላሉ።

"ቀድሞ ጫማ ቁጥሬን አላውቅም፤ ጫማም አድርጌ አላውቅም። ጫማ የሚባል ከእግሬ ገብቶ አያውቅም። ከተወለድኩኝ ጫማ አድርጌ አላውቅም። እኔ እግሬ ትልቅ ስለሆነ ነው። ሁሌም ጫማ ስለ ማላደርግ እግሬ ተሰነጣጥቋል። አሁን ግን ካልሲው አይቀር፤ ጫማው አይቀር ባይነት ባይነት እየቀያየርኩ ነው እግዜር ይስጥልኝ" ሲሉም ባለ ውለታዎቻቸውን ያመሰግናሉ።

የአቶ ብርሄ የቁመታቸውን ልክ ሲጠየቁ ማንበብም መጻፍም ስለማይችሉ ልኩ ስንት እንደሆነ ባያውቁትም፤ በተደጋጋሚ የለኳቸው ሰዎች ቁመታቸው 2 ነጥብ 50 ሜትር መድረሱን አረጋግጠውላቸዋል። ከቤተሰቦቻቸው መካከል እንደሳቸው አይነት ቁመት ያለው ሰው አለመኖሩን የሚናገሩት አቶ ብርሄ ቤተሰቦቻቸው "ቁመትህ እንደ ጓደኞችህ ቢሆን ዓይን ውስጥ አትገባም ነበር" እንደሚሏቸው ደጋግመው ይናገራሉ። ብዙ ጊዜ ቁመታቸው ልዩ በመሆኑ ካልሆነም ተወዳድሮ 'ልዩ ነገር' ማግኘት እንደነበረበት ሁሌም ያነሳሉ። በዚህ ምክንያትም 'ከሁለት አንድ ያጣህ ጎመን ሆንክ ይሉኛል' ብለዋል።

አቶ ብርሄ ጋሹ የትምህርት ቤትን ደጅ ረግጠው አያውቁም፤ የፊደል ዘር አልቆጠሩም። "ምክንያት?" ሲባሉ "ወላጆቼ ምስኪን ነበሩ" ሲሉ ይመልሳሉ። ከዘጠኝ ዓመት እድሜያቸው ጀምሮ ሰው ቤት ነው ያደጉት። "

ሕጻን ስለሆንኩኝ እናት አባቴን አገለግላለሁ በሚል እንጂ እንደዚህ እጉላላለሁ ብዬ አላሰብኩም። አሁን ግን አዝናለሁ፤ ብማር ኖሮ ራሴም አልጉላላም፤ ቤተሰቦቼንም እረዳ ነበር።" ይላሉ።

በቁመታቸው የተነሳ ካገኙት ነገር ይልቅ የተጎዱትን ማስታወስ ይወዳሉ። ከትዝታዎቻቸውም መካከል" ሁለት ጊዜ ወድቄ በተሰበርኩ ጊዜ፣ ቁመቴ ረዥም ባልሆን ብወድቅም እንኳን እነሳ ነበር። ብዙዎች አጠገቤ እየወደቁ ሳይሰበሩ ምንም ሳይሆኑ ይነሳሉ፤ አያቸዋለሁ። እኔ ግን ስወድቅ ሁለቱም ጊዜ አንዴ ቀኝ እጄን ሌላ ጊዜ ደግሞ ግራ ጫንቃዬን ተሰበርኩ። በዚህ በዚህ ቁመቴን አማርራለሁ። ሁለተኛው መሥራት ስችል ያለው ኅብረተሰብ እንዳሻው ሲያርስ እና ሲያጭድ ሳየው እና እኔ እንደዛ መሆን ሲያቅተኝ ስሜታዊ እሆንና እናደዳለሁ።" የሚሉት አቶ ብርሄ "ወይ ተምሬ እንደ ሰው ለቤተሰቦቼም ሆነ ለኔ ቀን አላወጣሁ፤ ወይም እንደ ሰው በጉልበቴ ሰርቼ አላድር ሁሉ ነገር ችግር ነው" ብለዋል።

"ረዥም በመሆንዎት ከሰው በተለየ የሚያገኙት ጥቅም ምንድነው?" ስንል ላነሳንላቸው ጥያቄ አቶ ብርሄ ሲመልሱ "አንዳንዴ ከላይ ያሉትን ነገሮች ሳወርድ ጥቅም ነው፤ ሌላው የማያወርደውን ሳወርድ ደስ ይላል። ከታች ያለውን ለማንሳት ነው እንጂ፤ ከላይ ያለውን ለማውረድ ለእኔ የላይኛው ስለሚቀርበኝ ለእኔ ደስ ይላል። አሁን ደግሞ ቀረጻ እና ቃለ መጠይቅ ሲደረግልኝ ተስፋ አለው መሰል ከሌላው ኅብረተሰብ ቁመቴ ስላደገ አይደል እላለሁ።" በማለት ነገ ብሩህ ተስፋ እንደሚታያቸው፤ ለእሳቸውም ሆነ ለልጆቻቸው የተሻለን ነገን የማግኘት ተስፋን ሰንቀው ያወጋሉ።

አቶ ብርሄ ባለትዳር ናቸው። የመጀመሪያ ልጃቸውን የወለደችላቸው ሚስታቸው አልፈልግም ብላ ጥላቸው ሄደች። ያኔ የመጀመሪያ ሚስታቸው ጋር እንደተለያዩ ብቸኝነት ሲያስከፋቸው ሥራ ፍለጋ ብለው ወደ አዲስ አበባ መጥተው እንደነበረ ያስታውሳሉ። ያኔ ሰው ምን ተዓምር መጣ ብለው ብርሄ ያረፈበትን ቤት ሰው ከቦት ነበር። ሊመለከታቸው ከየአቅጣጫው በርካታ ሰው ተሰበሰበ። በኋላ ፖሊስ ጋር ስልክ ተደውሎ በፖሊስ ሰው መበተኑን ያስታውሳሉ። የመጡበትን

ማህበራዊ

የሕይወት ገጽታ

ተፈጥሮ በስገሰቻቸው ቁመት ከመቸገር አልፈው እውቅና ያገኙት አቶ ብርሄን በኢቢኤስ ቴሌቪዥን በመመልከት ከሃገረ አሜሪካ ወደ ሃገሯ ኢትዮጵያ ለመምጣት ዝግጅት ስታደርግ የነበረችው ወይዘሮ ፍሬዘውድ ዮሐንስ ለወዳጅ ዘመድ ከሚሰጠው ስጦታ መካከል ለአቶ ብርሄም በልካቸው የሚሆን ጫማ ገዝታ ወደ ዝግጅት ክፍላችን ጎራ በማለት አበርክታላቸዋለች

ዓላማ ሳይዘነጉ ሥራ አግኝተው ቢጀምሩም እንደ ልዩ ፍጥረት በመታየታቸው ከቀናት በላይ መቆየት ተስኗቸው ወደ ትውልድ ቀያቸው መመለሳቸውን ያስታውሳሉ።

ከዚህ በኋላም በድጋሚ ሚስት ለማግባት ፈልገው ያጫሉ። ያጨትም በርዝመታቸው የተነሳ አልፈልግም በማለት ወደ ኋላ ትላለች። በኋላም ተስፋ ባለመቁረጥ ውህ አጣጫቸውን የፈለጉት አቶ በርሄ አሁን አብራቸው ያለችውን ሚስታቸውን አጨ፤ ይህች ሴት ላለማግባት ብታንገራግርም ቤተሰቦቿ አሳምነዋት በትዳር ለመጣመር በቁ። አሁን ካገቧት ሚስታቸው ጋር ሦስት ወንድ ልጆች አፍርተዋል። አቶ ብርሄ የአንድ ሴት እና የሶሰት ወንዶች በድምሩ የአራት ልጆች አባት ለመሆን በቅቷል።

እንደ አቶ ብርሄ ገለፃ "ማረስ፣ ማጨድ እና ማረም አልችም። የሚያስቸግረኝ በጣም ዝቅ ስል ወገቤ እና አንገቴ ይወጣና ስሜታዊ ያደረግኛል" ይላሉ። እንዲህም ቢሆን መተዳደሪያቸው እርሻ ነው። ለዚህም ባለቤታቸውን ያመሰግናሉ።" ባለቤቴ ሁሉንም ትሠራለች። ጎረቤቶቼም በእርሻ ሥራ ከጎኔ አልተለዩም። አንዳንዴ ግን ሥራ በዝቶባት እንደ ሌሎቹ ባሎች ረዳት ልሆናት ሳልችል ስቀር ቢከፋትም ሁሉን እሷ ይዛ ነው የምንኖር።" "አሁን ያለችው ሚስቴ በአጨዳው በምኑ ሥራ ሲበዛባት አንዳንዴ እንዲህ ሆነህ [ቁመትህ ረዝሞ] ተቸግረህ እኔም ተቸግሬ ብላ ይሰማታል እንጂ ከዛ ውጭ ፍቅረኛ ነን።" በማለት ያመሰግናሉ።

"ማኅበረሰቡ በሙሉ እንደዚህ ሆንክ በሚል ለእኔ መንግሥት ድጋፍ ቢያደርግልህ እያለ የሚቆረቆር ነው። በአጨዳም ሆነ በእርሻ ያግዘኛል። በልማት እና በጥበቃም አያዘኝም። የኔን ኮታ ኅብረተሰቡ ነው የሚሸፍነው።" በማለት አቶ ብርሄ የአካባቢያቸውን ማኅበረሰብ ያመሰግናሉ።

"መኖሪያ ቤትዎት የተለየ ነው ወይ? አልጋዎትስ ምን ይመስላል?" ስንል ላነሳንላቸው ጥያቄ አቶ ብርሄ ምላሽ ሲሰጡ "እኔ የምኖርበት ቤት እንደ ኅብረተሰቡ ነው የተሠራው። በሩም ተመሳሳይ ነው። ስገባ እና ስወጣ እያጎነበስኩኝ ነው።" ይላሉ። "የምተኛበት አልጋ ግን ከሌሎች ረዘም ተደርጎ ተሠርቶልኛል፤ እንዲያ ባይሆን እግሬ መሬት ሲጠርግ ነበር የሚያድር።" ብለዋል። "ሌላ አልጋ ላይ ስተኛ በአንድ በኩል በጣም ይተርፋል።"

ፈራ ተባ እያልኩኝ "ፆታዊ ግንኙነትስ እንዴት ነው? አልኩኝ። መጀመሪያ ረዘም ያለ ሳቅን አስቀድመው "በዛ ጉዳይ ላይ ደግሞ ወገል እና ማረሻ ከተገጣጠመ ችግር የለውም።" የሚል በፈገግታ የታጀበ ምላሽ አግኝቻለሁ።

"ግን ሴቶቹ አላገባህም የሚሉት ለምን ይመስልዎታል?" "እምቢ የሚሉት ረዥም ነው ሠርቶ አያበላንም። አንዳንዱ ደግሞ ይኼን ሰውዬ አያችሁት እያለ ስለሚስቅ ስለሚሳቅባቸው ነውር ይመስላቸዋል። ለዛም ነው እንጂ ከሰው የተለየ ምን ፍጥረት ሆኜ ነው?" በማለት ጥያቄዬን በጥያቄ ይመልሳሉ።

በዘራቸው ውስጥ እንደሳቸው ረዥም ቁመት ያለው በቤተሰቡ ውስጥ አለመኖሩን የሚናገሩት አቶ ብርሄ "የኔ ፍጥረት የተለየ በመሆኑ ቆሜ ሌሎች የማያዩትን ነገር አያለሁ። ፈቀቅ ያለ ከማዶ ወደ ተራራ አካባቢ ሌሎች የማያዩትን እኔ ማየት እችላለሁ" በማለት ያስረዳሉ።

"ከልጆችዎትስ መሐል በእርስዎ የወጣ ይኖር ይሆን?" ስንል ለሰነዘርነው ጥያቄ ምላሽ የሰጡት አቶ ብርሄ ሴቷ ልጃቸው ረዥም እንደምትሆን እንደሚገምቱ ይናገራሉ። "የመጀመሪያ ሴት ልጄ አገዳዋን ሳየው እንደኔ ባትሆንም ረዥም ነው። 10 ዓመቷ ነው፤ ሳየው አገዳዋ፣ ጣቷ፣ አንጓዋንና እጇን . . . ሁኔታዋን ሳየው ረዥም ትመስለኛለች። ሌላው ወገኔን ሳየው አጭር ነው። እንደ እኔ ቀርቶ የኔን ግማሽ አይሆንም" ብለዋል።

"ልጆቼ ጨቅላ ናቸው፤ ጨቅላ ስለሆኑ፣ ገና ትንሽ ስለሆኑ ረዥም ይሁኑ አጭር ብዙም ገንዘብ ብለን ለማወቅ ይቸግረናል። ያው ብቻ በጣም ይወዱኛል። ለትንሽ ደቂቃ ተለይቻቸው ስመጣ ብርቀኛ ሆነው መጣ መጣ እያሉ ይደሰታሉ።" በማለት ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር ኃያል መሆኑን ይናገራሉ።

"አቶ ብርሄ እንደው በዚህ ቁመቱ ምክንያት ምን ገጥሞት ይሆን?" በማለት ላቀረብንላቸው ጥያቄ እንዲህ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። "አንዲቱ ገበያ እያለሁ ከታች እግሬን ቆነጠጠችኝ። ዞር ብዬ ሳያት 'ለካ ይሄ ሰውዬ ይሰማል' ብላኛለች። በዚህ በዚህ ይሰማኛል።" "ፀባዩ ጥሩ ነው። በዚህ ቁመቱ ክፉ ቢሆን ሰው ይረብሽ ነበር " በማለት ሰዎች እንደልዩ ፍጥረት መመልከታቸው ቅሬታ የሚፈጥርባቸው መሆኑን ነው የተናገሩት።

የአቶ ብርሄ ሌላው ፈተና ትራንስፖርት ነው። "መኪና ላይ ወንበሩ እግሬን ስለማይመቸኝ ዳር ላይ ሆኜ እንጂ እንዳሻኝ አልሆንም። ሾፌሮች እና ረዳቶች የሁለት ሰው ቦታ ስለምትይዝ የሁለት ሰው መክፈል ነበረብህ ይሉኛል።" "ሁለት ሰው ይዘን ነበር የምንሄደው እያሉ ገበያም ስንሄድ ሞተረኞች የሁለት ሰው ይቀበሉኛል" ።

አቶ ብርሄ ጋሹ እድሜያቸው ሰላሳ ስምንት በመድረሱ ከዚህ በኋላ ቁመቴ ይጨምራል ብለው እንደማያስቡ ይናገራሉ። ለወደ ፊት የቁመት ውድድር መወዳደር ይፈልጋሉ። "የወደፊት ዕቅዴ ተወዳድሮ ማሸነፍ ነው። ተወዳድሬ ከኢትዮጵያ አንደኛ መውጣት አለብኝ። አሁንም አንደኛ ነኝ። ተወዳድሬ ማሸነፍ አለብኝ ነው እቅዴ።" በማለት በቁመታቸው መታወቅ የሚፈልጉ መሆኑን ያስረዳሉ።

ቁመታቸው በመርዘሙ ከሰው የተለየ ምግብ ብዙም እንደማይበሉ የሚናገሩት አቶ ብርሄ "መጠጥ ግን በደንብ ነው የምጠጣው። እኛ ሃገር የሚጠጣው ጠላ ነው። ምንም በጠጣ ሽንቱ እስካላስቸገረኝ ድረስ አይበግረኝም።" ብለዋል።

አቶ ብርሄ በሰዎች አይንና ልብ ከገቡ በኋላ በርካቶች እሳቸውን ማነጋገር፤ ፕሮግራም መሥራትና ሌሎችም ጉዳዮች እየተከናወኑ በመሆኑ ብዙዎቹ በገንዘብ፣ በአልባሳት ... ድጋፍ እያደረጉላቸው ይገኛል። የሁል ጊዜም ህልማቸው የሆነውን ገንዘብ አግኝተው ልጆቻቸውን በአግባቡ ማልበስ ጥያቄም በደጋግ እጆች እየተመለሰ መሆኑን ይናገራሉ።

"ለወደፊት በቁመት ውድድር ተወዳድሬ ገንዘብ ባገኝ ልጆቼን በወግ ባስተምር ደስ ይለኛል፤ ገጠርም ያው ሥራውን እኔ ስላልቻልኩት ከተማ አካባቢ ቦታ ተሰጥቶኝ ብኖር" የሚል ጥያቄ አላቸው።

"ሰው ካወቆት በኋላ በአኗኗርዎት ላይ ምን ተቀየረ?" ስንል ላቀረብንላቸው ጥያቄ "መጀመሪያ የወገኔን ደግነት ተመልክቼበታለሁ፤ ሁሉም ሰው ለሰው ፍቅር እንዳለው አይቻለሁ፤ የከተማ ሰው በሩን ዘግቶ ነው የሚበላው ሲባል እውነት ይመስለኝ ነበር። ግን ሁሉም ሰው ደግ ነው" የሚል ምላሽ የሰጡት አቶ ብርሄ በተለያዩ አካላት የገንዘብም፣ የቁሳቁስም ድጋፍ እንደተደረገላቸው ይናገራሉ።" በተለያየ ጊዜ ቀረፃ እያደረጉ ለሰው ላስተዋወቁኝ፤ ፕሮግራሞችንም ተመልክተው እጃቸውን ለዘረጉልኝ በሙሉ አመሰግናለሁ።" በማለት የነበረንን ቆይታ አጠናቀናል።

ተፈጥሮ በለገሰቻቸው ቁመት ከመቸገር አልፈው እውቅና ያገኙት አቶ ብርሄን በኢቢኤስ ቴሌቪዥን በመመልከት ከሃገረ አሜሪካ ወደ ሃገሯ ኢትዮጵያ ለመምጣት ዝግጅት ስታደርግ የነበረችው ወይዘሮ ፍሬዘውድ ዮሐንስ ለወዳጅ ዘመድ ከሚሰጠው ስጦታ መካከል ለአቶ ብርሄም በልካቸው የሚሆን ጫማ ገዝታ ወደ ዝግጅት ክፍላችን ጎራ በማለት አበርክታላቸዋለች።

ወይዘሮ ፍሬዘውድ ለመጀመሪያ ጊዜ እኚህን ሰው ስትመለከት "አሜሪካ ቢሆኑ እንዴት ያሉ ባስኬት ቦል (ቅርጫት ኳስ) ተጫዋች ይወጣቸው ነበር" ብላ ማሰቧን ትናገራለች። በሃገሯ በዚህ ልክ ረጅም ሰው መኖሩ ቢያስደንቃትም ባዶ እግራቸውን መሆናቸው አሳዝኗት ስጦታውን ለመግዛት ማሰቧን ትናገራለች። እሳቸውም ክብረት ይስጥልኝ በሚል ምርቃት ስጦታቸውን ተቀብለዋል።

እኛም ሀሳባቸው ይሙላ፤ ያሰቡት ይሳካላቸው። በማለት ከመለሎው አቶ ብርሄ ጋሹ ጋር የነበረንን ለዛ ያለው ጨዋታ አብቀተናል።

ኢኮኖሚ

ባህልና ቱሪዝም

“ፋቼ ጨምባላላ” ባህላዊ ምሰሶ

ዳግም ከበደ

ሀዋሳ ከወትሮው በተለየ መንገድ ደማቅ ሆናለች። ምክንያቱ ደግሞ በየዓመቱ ተከብሮ የሚውለውን የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ ፍቼ ጫምባላላ ክብረ በዓልን አስመልክቶ ነው። ወጣቶች፣ እናቶችና ሽማግሌዎች የማኅበረሰቡን እሴቶች የሚገልፁ አልባሳት፣ የፀጉር አሠራር፣ ምግቦችና ጭፈራዎች አዘጋጅተው ከምንግዜውም በተለየ መንገድ እንድትደምቅ አድርገዋታል። የፍቼ ጫምባላላ በዓል ከክልሉ አልፎ የአገርና የዓለም የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ሆኖ የተመዘገበ እንደመሆኑ ቀኑ ሲደርስ ሁሉም በከተማዋ ተገኝቶ ዋናው ሥነሥርዓት በሚከበርበት “ጉዱማሌ” በተባለ ሰፊ ስፍራ ላይ ያከብረዋል።

የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ ፍቼና አዲሱ ዓመት ክብረ በዓል መንፈሳዊ (ኢንታንጀብል) ባህል ከሆኑት አንዱ ሲሆን፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሻገር የመጣ የብሔሩ ማንነት መገለጫ መሆኑ ይታወቃል። በሲዳማ ሕዝብ ፍቼና ጫምባላላ የማይነጣጠሉ የበዓሉ ሁነቶች ናቸው፡፡ ፍቼ የአሮጌው ዘመን መጠናቀቅ (ዋዜማ) ጫምባላላ የአዲሱ ዘመን (መባቻ) ብስራቶች መሆኑን የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ አበበ ታፈሰ ለዝግጅት ክፍላችን ነግረውናል፡፡ ከዚህ እንደሚከተለው የ”ፍቼንና” የ”ጫምባላላን” ጥቂት እውነታዎች እናጋራችሁ

ፍቼ የአሮጌው ዓመት መጨረሻ የአዲሱ ዋዜማ እንደመሆኑ የብሔሩ ሊቃውንት የጨረቃና ኮከብ አቅጣጫና ቁጥር ተመልክተው የዘመን መለወጫ ትክክለኛ ወሩንና ቀኑን ከወሰኑ በኋላ ለሕዝቡ ከአንድ ሳምንት በፊት በገበያ ይታወጃል፡፡ የዘመን መለወጫ ቀኑ ከታወጀ በኋላ የብሔሩ ባህላዊ መሪዎች (ዎማች) ለፍቼ ሳምንት ሲቀረው ከአንድ ወር በፊት የጀመሩት ጾምና የሱባኤ (የንስሐ) ጸሎታቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡ ሴቶች ለበዓሉ ማድመቂያ ቅቤ፣ ቆጮ፣ ወተትና ቅመማቅመም ያዘጋጃሉ፡ ፡ ወጣት ወንዶች እንጨት ወጣት ሴቶች ለእናታቸውና ረዳት ለሌላቸው ጎረቤቶች የሚያቀርቡበትና የሚረዱበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ዋዜማን ከደረሱ በኋላ በእርጥብ ቅጠል የተዘጋጀ መሸሎኪያ (ሁሉቃ) ፀሐይ ስታዘቀዝቅ የቤተሰቡ አባላትና ከብቶች በዚያ ሾልከው እንዲያልፉ ይደረጋል፡ ፡ ጫምባላላ (ዞሮ መምጣት ማለት ነው) አዲሱ ዓመት የሚጀመርበት ልጆች ምንም ሥራ የማይሠሩበትና እየዞሩ የሚመገቡበት፣ ከብቶች ለዚህ ቀን ተከልሎ በቆየ ጥብቅ(በረት) ውስጥ ተለቀው የሚግጡበት ቀን ነው፡፡ ልጆቹ «አይዴ ጫምባላላ»(ዞረን መጣን) እያሉ ተስብስበው በየአካባቢው ሲዞሩ እናቶች «እሌ...እሌ..»፣ ወይም «ድረሱ....ድረሱ» በማለት በቅቤ የተዘጋጀውን ቆጮ (ቡሪሳሜ) ያቀርቡላቸውና ይበላሉ፡፡

ፎቶ፡ ሐዲስ አበርሃ

ፍቼ ጨምበላላ በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፣

የፍቼ በዓል ሁሌም በብሔሩ የሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን ማለትም በቃዋዶ ቢውልም ቀኑ በየዓመቱ በተመሳሳይ ቀን ስለማይውል መች እንደሚውል ተለይቶ የሚታወቀው በባህላዊ ቀን ቆጠራ ስሌትና የሥነ ከዋክብት ምልከታ ነው

የዘንድሮው የፍቼ በዓል አከባበር

የሲዳማ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄ ለዘመናት ሲያነሳ ቆይቶ አሁን ጥያቄዎቹ ተመልሰውለት የኢትዮጵያ አስረኛ ክልል መሆን ችሏል። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ማኅበረሰቡ ቋንቋውን ባህሉንና ሌሎች ታሪካዊ ሃብቶቹን ጠብቆና አስተዋውቆ ማሳደግ እንዲችል ከምን ግዜውም በላይ እድል እንደፈጠረለት እየተነገረ ይገኛል።

የዘንድሮው አከባበር ሥነ ሥርዓትም ይህን ድባብና ድርብ ድል ታሳቢ አድርጎ በድምቀት ሊከበር ችሏል። ከከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት፣ የገዳ መሪዎች፣ ሽማግሌዎችና የአገር ውስጥና የውጪ ጎብኚዎችም በዚህ የፍቼ ጫምባላላ በዓል ላይ ተሳታፊ ነበሩ።

በዩኒስኮ በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ የዓለም ባህላዊና መንፈሳዊ ሃብት ሆኖ የተመዘገበው ይህ ሃብት በርካታ ገፅታዎችና በውስጡ ጠብቆ ያቆያቸው እሴቶችን የያዘ ነው። በመሠረታዊነት “የፍቼና” የ”ጫምባላላ” በዓላት ዋንኞቹ ሥነሥርዓቶች ሲሆኑ፣የአሮጌውን ዓመት ሽኝት እና የአዲሱን ዓመት አቀባበል ይወክላሉ። ከዚህ በመነሳት በዘንድሮው የሲዳማ ብሔር መገለጫ ባህል ላይ የፍቼ (ዋዜማ) ሥነሥርዓት ልዩ ልዩ እንግዶች በተገኙበት ተከብሮ አልፏል።

የሲዳማ ብሔር የአዲስ ዘመን መለወጫ ዋዜማ የሆነው የ”ፍቼ” (ዋዜማ) በሲዳማ የባህል አዳራሽ ነበር ሥነሥርዓት የተከናወነው። በፍቼ የዋዜማ ክብረ በዓል ላይ የተገኙት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ደስታ ሌዳሞ “የፍቼ ጨምባላላ በዓል ለሲዳማ ሕዝብ ታላቅ በዓል ነው” በማለት ለብሔረሰቡም ሆነ ለመላው ኢትዮጵያ ያለውን ትርጉም ተናግረው ነበር። በተለይ በውስጡ የያዛቸው እሴቶች የአገር በቀል እውቀቶችን ሲሆን የአንድነት፣የእርቅ የመተሳሰብ ተምሳሌት መሆናቸውን ጠቅሰው እነዚህን ሃብቶች ለኢትዮጵያውያን ታላቅ ስጦታ እንደሆኑ ይገልፃሉ። ከመቼውም ግዜ በተለየ የፍቼ ጨምባላላ የሚፈቅደውን ወንድማማችነት፣ አንድነትና ፍቅር መሠረት በማድረግ መላው ኢትዮጵያዊ ሕብረቱን ለማጠናከር የሚፈጥረው እሴትም ጉልህ እንደሆነ ይናገራሉ። በአዲሱ የዘመን መለወጫም አዲስ አስተሳሰብና ፍቅርን መላበስ እንደሚያስፈልግ አንስተው የፍቼ ጫምባላላ ዋነኛ መሠረትም ይህ እንደሆነ ተናግረዋል።

“የዘንድሮውን የፍቼ ጫምባላላ በዓል ስናከብር ደስታችን እጥፍ ድርብ ሆኖ ነው” ያሉት የክልሉ ፕሬዚዳንት፤ የሲዳማ ሕዝብ ጥያቄዎች የተመለሱበት በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል በማለት በፍቼ የዋዜማ ክብረ በዓል ላይ በሲዳማ የባህል አዳራሽ ለተገኙ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳን ጨምሮ ከአንድ ሺህ 100 በላይ ተሳታፊዎች የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። ከፌደራል እና ከክልሎች የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ እንግዶችና ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት በፍቼ የዋዜማ ሥነ ሥርዓት ላይ መሳተፋቸው ከዚህ ቀደም ከነበረው በተለየ መንገድ በዓሉ ልዩ ይዘትና ድምቀት እንዲኖረው አድርጎት አልፏል።

ባህላዊ መሪዎች

በዘንድሮው የፍቼ ጫምባላላ በዋነኝነት በብሔሩ ባህላዊ መሪዎች (ዎማች) በፍቼ ዋዜማና በጨምባላላ በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ላይ ተገኝተው ባህላዊ ምርቃት የሚሰጡበት ሲሆን፣በተለይ በዋዜማው ዕለት በባህሉ መሠረት የሚከናወን በእርጥብ ቅጠል የተዘጋጀ መሹለኪያ (ሁሉቅ) ውስጥ የማለፍ ሥነሥርዓት አካሂደዋል። በፍቼ በዓል ላይ ሻፈታ በጋራ ተቆርሶ የተቀመሰ ሲሆን፣ልዩ ልዩ ባህላዊ ሥነሥርዓትም ተከናውናል።

በሀዋሳ ጉዱማሌ የጫምባላላ የአዲስ ዘመን መለወጫ በተከበረበት ወቅት በስፍራው የተገኙት የባህል ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ ይህን ታላቅ የሲዳማ ሕዝብ መገለጫ አስመልክተው ሲናገሩ የፍቼ ጫምባላላ በዓል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ በሲዳማ ብሔር አባላት ዘንድ በየዓመቱ በድምቀት የሚከበር የዘመን መለወጫ በዓል መሆኑን አንስተዋል፡፡ በዓሉ በቤተሰብና በጎረቤት ደረጃ ተሰባስቦ በማክበር የሚጀምርና ከዚያም እየሰፋ በመሄድ በባህላዊ አደባባይ (ጉዱማሌ) በጋራ የማክበር ሒደትን የሚያጠቃልል ነው በማለትም ከወንድም ሕዝቡ የኦሮሞ የኢሬቻ ሥነሥርዓት ጋርም ብዙ የሚያመሳስለው ሥነሥርዓቶች እንዳሉት አስረድተዋል፡፡

ፍቼ ከዘመን መለወጫ በዓልነት ፋይዳው ባሻገር በርካታ ባህላዊና ማኅበራዊ ፋይዳዎች ያሉት መሆኑን በመግለፅም ፣ ሃገር በቀል የሆነ የዘመን አቆጣጠር ዕውቀትን አካቶ ከመያዙ ባሻገር የሲዳማ ብሔር አንኳር የሆኑ ባህላዊ ገጽታዎች የሚንፀባረቁበት ኢንታንጀብል (ግዙፍነት የሌለው ወይም የማይዳሰስ) ቅርስ መሆኑን መስከረዋል፡፡ የፍቼ በዓል ሰላም፣ መከባበር፣ መቻቻል እንዲሰፍን፣ ዕርቅ እንዲወርድ እንዲሁም ልማት እንዲፋጠንና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የኃሳ መሪዎችና የበቁ አረጋውያን ለጎብረተሰቡ በሰፊው ትምህርት የሚሰጡበት ወቅት ከመሆኑ አንፃር ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ይህን ታላቅ ባህላዊ ሥርዓት ለመጠበቅ፣ ለማልማትና ለማስተዋወቅ ከመቼውም ጊዜ በላይ እንደሚሠራ ቃል ገብተዋል፡፡

የፍቼ በዓል አፈ ታሪክ

የፍቼ በዓል በአፈ ታሪክ እንደሚወሳው መጠሪያውን ያገኘው ፊቾ ከምትባል የሲዳማ ሴት ነው፡፡ ፊቾ ዕድሜዋ ለአቅመ ሔዋን ሲደርስ በሲዳማ ብሔር ባህልና ሥርዓት መሠረት ተዳረች፡፡ ይህች ሴት በየዓመቱ ለወላጆቿ፣ ወንድሞቿ፣ ለዘመድ አዝማድና ጎረቤት ቡርሳሜ (ከእንሰት ላይ የሚፋቅ ቆጮ በእሳት ላይ ተነኩሮ እና ቅቤ በብዛት ተጨምሮበት የሚዘጋጅ ባሕላዊ ምግብ) እና እርጎ በመያዝ በየዓመቱ በሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ በዓል በሚውልበት ዕለት በቋሚነት ትጠይቃቸው ነበር፡፡ በዓሉ የሚውለው በተመሳሳይ ቃዋዶ (በሲዳማ ብሔር የቀን አቆጣጠር የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን) ሲሆን፣በአፈ ታሪኩ መሠረት ፊቾ ያመጣቸውንም ምግብ በዚሁ ዕለት ምሽት ላይ ዘመድ አዝማድ፣ የአካባቢ ጎረቤትና ቤተሰብ ተሰባስበው ይመገቡት ነበር፡፡ አባቷና ታዳሚዎች ዘወትር የፊቾን ደግነትና ያመጣቸውን ምግብ በማድነቅ ይመርቋታል፡፡ ፊቾ ይህንን በተደጋጋሚ ስትፈጽም ቆይታ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ የአካባቢው ነዋሪዎች ፊቾ በመሞቷ ጥልቅ ሐዘን የተሰማቸው ከመሆኑም በላይ የሷ ድግስ ታዳሚ የነበሩ ሰዎች ይህችን ሩህሩህ ደስታ ፈጣሪ ሴት በዘላቂነት ለማስታወስ ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል እርሷ ምግብ ይዛ የምትመጣበትንና ግብጥጥው የሚካሄድበትን የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ ቀን በስሟ ፍቼ ብለው ሰየሙት፡፡ የፍቼ በዓል ሁሌም በቃዋዶ ቀን የሚውልበት ምክንያት ቀኑ በብሔሩ የሳምንቱ የመጀመሪያውና ታላቅ ቀን ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ ነው፡፡

ማኅበራዊ ክንዋኔዎች

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ አበበ ታፈሰ የጫምባላላን ማኅበራዊና ባህላዊ ክንዋኔ ከዚህ እንደሚከተለው አብራርተውልናል።

የሲዳማ ብሔር ዘመን መለወጫ በዓል የሆነው ፍቼ ለሁለት ሳምንታት ያህል በድምቀት የሚከበር ሲሆን አከባበሩም ቅደም ተከተላዊ ሥርዓትና ሂደት ያለው ነው፡፡ ከነዚህ ማኅበራዊ ክንዋኔዎች መካከል የመጀመሪያው ላኦ (ምልከታ) ነው፡፡ የፍቼ በዓል ሁሌም በብሔሩ የሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን ማለትም በቃዋዶ ቢውልም ቀኑ በየዓመቱ በተመሳሳይ ቀን ስለማይውል መቼ እንደሚውል ተለይቶ የሚታወቀው በባህላዊ ቀን ቆጠራ ስሌትና የሥነ ከዋክብት ምልከታ ነው፡፡ የሥነ ከዋክብት ምልከታውን የሚያከናውኑት አያንቶ የተሰኙ የሥነ ከዋክብት ጠበብቶች ናቸው፡፡ አያንቶዎች ቡሳ የተሰኙ ኅብረ ከዋክብት ከጨረቃ አቀማመጥ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማገናዘብ ማለትም የከዋክብቱ ከጨረቃ የመቅደምና ወደ ኋላ የመቅረት ሁኔታ በትኩረት በመከታተል በተለይ ከከዋክብቱ መካከል አውራ የሆነችው ኮከብ ከጨረቃ መቅደሟን ሲያረጋግጡ ፍቼ በቀጣይ ቀናት ውስጥ ባለው የቃዋዶ ዕለት እንደሚውል ይወስናሉ፡፡

ከዚያም የሥነ ከዋክብት ምልከታውን የሚያከናውኑት አያንቶዎች የፍቼ በዓል የሚውልበትን ቀን ለኃሳ መሪዎች (ገሮ) ያሳውቃሉ፡፡ አያንቶዎች ባቀረቡት ሐሳብ ላይ ተመሥርተው የኃሳ መሪዎች ከጪሜሳዎች (የበቁ አረጋውያን) ጋር ሶንሳ (የአዛውንቶች ስብሰባ) በማድረግ በጉዳዩ ላይ ከተወያዩ በኋላ ቀኑ በአዋጅ ለኅብረተሰቡ እንዲገለጽ ከስምምነት ይደርሳሉ፡፡ የኃሳ መሪዎችም በየአካባቢያቸው በሚገኙ የገበያ ሥፍራዎች የበግ ቆዳ ረዥም ዘንግ ላይ ሰቅለው በመያዝ ለኅብረተሰቡ የፍቼ በዓል የሚውልበትን ቀን ያውጃሉ (ላላዋ ያደርጋሉ)፡፡ ከላላዋ በኋላ ሳፎቴ ቄጣላ (የመጀመሪያው ባህላዊ ጭፈራ) ይቀጥላል፡፡

ፍቼ ጫምባላላ ከሲዳማ ብሔር ባህላዊ ሃብትነት ባሻገር በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣የሳይንስና የባህል ድርጅት(ዩኔስኮ) የማይዳሰስ መንፈሳዊ ሃብትነት ከተመዘገቡ የኢትዮጵያ ሃብቶች መካከል የሚመደብ ነው። እንደሌሎቹ መሰል የአደባባይ በዓላት ሁሉ ይህ ታላቅ ባህልም ለሕዝቦች አንድነት፣ መተሳሰብና ፍቅር ምሰሶ በመሆኑ ልናለማው፣ ልንጠብቀውና በተገቢው መንገድ ለትውልድ እንዲሻገር ልናስተዋውቀው እንደሚገባ ጠቁመን ሃሳባችንን እዚህ ላይ እንቋጫለን።

ስፖርት እና መዝናኛ

ሳምንቱን በታሪክ

የብዙዎችን መብት ያስከበረው ቀን

ዋስልኝ አየለ

ይህ ቀን የተለያዩ ስያሜዎች አሉት። የላብ አደሮች ቀን፣ የወዝ አደሮች ቀን፣ የሠራተኞች ቀን እየተባለም ሲገልጽ ኖሯል። የሁሉም ቃላት ትርጉሞች ተመሳሳይና የኢንዱስትሪ ሠራተኛውን የሚመለከቱ ናቸው። በብዛት የላብ አደሮች ቀን በመባል የሚታወቅ ቢሆንም፣ በተለይ በሃገራችን የሠራተኞች ቀን በሚል ሲከበር ቆይቷል። በውጪዎቹ ሃገሮች ደግሞ ደግሞ May day እና Labor day በመባል ይታወቃል። እነዚህም የኢንዱስትሪ ሠራተኛውን የሚመለከቱ ናቸው።

ቀኑ በኢትዮጵያ በስፋት መከበር ከጀመረበት ከየካቲት 1966 ዓ.ም አብዮት ወዲህ በተለያየ ስያሜዎች ሲጠራ ቢቆይም ከዚያው ከደርግ ዘመን አንስቶ የሠራተኞች ቀን እየተባለ ይጠራል። የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ማኅበራትን ይዞ ከተመሠረተው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን በመነሳት ስንመለከተውም ቀኑ የሠራተኞች ቀን መሆኑን እንረዳለን።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ይህን የሠራተኞች ቀን እናስታውሳለን። አጋጣሚ ሆኖ ደግሞ ቀኑ ዛሬ ሆነና ዕለቱን በታሪክም አስመስለውታል። እነሆ ስለዚህ ቀን ዓለም አቀፋዊና አገር አቀፋዊ ሁኔታዎች ከተለያዩ ሰነዶች ያገኘናቸውን መረጃዎች በማሰባሰብ ምን እንደነበርና አሁን ምን ላይ እንዳለ እናስታውሳለን። በዚህ አጋጣሚ በዚህ ዓመት የሚከበረው በአገራችን ለ47ኛ ጊዜ ነው። በዓለም ደግሞ ለ133 ጊዜ ነው። የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን፣ የዓለም የኢንዱስትሪ ሰራተኞች (Industrial Workers of the World) የተሰኘው ዓለም አቀፍ ድረ ገጽ እና የሐበሻ ጊዜ የአማርኛ ጦማር ሰነዶችን ያገኘንባቸው ናቸው።

የላብ አደሮች ወይም የሠራተኞች ቀን ሲባል ወደብዙዎች አዕምሮ የሚመጣው የሶሻሊስት ሥርዓት ነው። የሚገርመው ግን ይህ ንቅናቄ የተጀመረው በካፒታሊስት አገሮች መሆኑ ነው። በኋላ ላይ ግን የሶሻሊስት ሥርዓት አቀንቃኞች አጠናክረው አስቀጠሉት። ለሶሻሊስት ሥርዓት መጠናከርም ፈር ቀዳጅ ሆነ። በኢትዮጵያም ብዙ ሰው ቀኑን የሚያስታውሰው የሶሻሊስት ሥርዓት አራማጅ ከነበረው በ1966ቱ አብዮት ወደ ስልጣን ከመጣው ከደርግ መንግሥት ጋር በማያያዝ ነው።

የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ፤ ሠራተኛው መደብ በቀን የሚሠራበት ሰዓት ከስምንት ሰዓት እንዳይበልጥ ከፍተኛ ትግል ማድረግ የጀመረበት ወቅት ነበር። በዘመኑ በቀን ከ10 እስከ 16 ሰዓት ለሥራ ምቹ ባልሆኑ አካባቢዎች ለአደጋ ተጋልጦ መሥራት የተለመደ ነበር። በሥራ ላይ በሚደርስ አደጋ ሕይወትን ማጣት፣ አካል መጉደል፣ ለዘላቂ የጤና ችግር መዳረግም የተለመዱ ሁኔታዎች እንደነበሩ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ1860ዎቹ ሠራተኞች የሥራ ሰዓት በቀን ስምንት ሰዓት ብቻ ሆኖ የሙሉ ቀን ደመወዝ እንዲከፈላቸው ባልተደራጀ መልኩ መጠየቅ ጀመሩ። ነገር ግን የዘመኑ ከበርቴዎች ለጥያቄው ምላሽ መስጠት አልፈለጉም። ይህም ሠራተኞች እንዲደራጁና ከፍተኛ ትግልና ተጋድሎ እንዲያደርጉ በር ከፈተ። ቀጣሪዎች በቀን ለረዥም ሰዓታት በማሠራት ከፍተኛ ትርፍ ማግኘትን ብቻ የለመዱ በመሆናቸው የሠራተኞችን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኞች አልሆኑም። ጥያቄው ግን የበለጠ እየተጠናከረ መጣ።

ጥያቄው እየተጠናከረ ሲመጣ በወቅቱ ከከበርቴዎች ከፍተኛ ነቀፌታ አጋጠመው። ሠራተኞችም ብዙ መስዋዕት ከፍለዋል። «አድማ አስነስታችኋል፤ ምርታማነታችን ቀንሳል፤ እኛ ቀጣሪዎች በምንፈልገው መጠን ካልሠራችሁ አንፈልጋችሁም» እየተባሉ ከሥራ ተሰናብተዋል። ከ20 ዓመታት መራር ተጋድሎ በኋላ ግን የሠራተኛው መደብ የድል ጮራን ማሳየት ጀመረ።

ሠራተኞች ይህን እንቅስቃሴ ሲጀምሩ፤ ዘመኑ ሶሻሊዝም እንደ አዲስ ያቆጠቆጠበት፣ ለሠራተኛው መደብ እጅግ ምቹ የሆነ ርዕዮተ ዓለም የሰፈነበት ነበር። ሶሻሊዝም ደግሞ ከግል ይልቅ ለጋራ ሀብት ትኩረት የሚሰጥ፣ መብቶችን በጋራ ለማስከበር የሚሞክር፣ በአብዛኛው በሩሲያ፣ ኩባና ሰሜን ኮርያ በሰፊው ሲቀነቀን የኖረ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ነው።

በመንግሥትና በአሠሪ ከበርቴዎች ሰዎች በቀን ስስምንት ሰዓታት ብቻ መሥራት እንዳለባቸው ታመነ፤ ተወሰነ:: ቅዳሜም እንደ እሑድ ሁሉ የሳምንቱ የእረፍት ቀን ሆነ:: በዚህ የተነሳ ሚያዝያ 23 ቀን በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ደግሞ ግንቦት አንድ ቀን የዓለም የሠራተኞች ቀን እየተባለ ለሠራተኞች መብት ሕይወት የከፈሉ ሰዎች የሚታሰቡበት ሆነ

አብዛኞቹ ሠራተኞች የምርቱ ተቆጣጣሪ፣ አከፋፋይና ተጠቃሚ መሆን አለባቸው» የሚል አስተሳሰብ ውስጥ የገቡበት ጊዜ ነበር። በብዙዎች ላብ ጥቂቶች የሚጠቀሙበት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞች እየሞቱና እየቆሰሉ ጥቂቶች ትርፍ የሚያጋብሱበት ካፒታሊዝም አያስፈልገንም የሚሉት ሠራተኞች ናቸው ሶሻሊዝምን እንደ አዲስ አማራጭ ማቀንቀን የጀመሩት።

ካፒታሊዝም ደግሞ ግለኝነትን የሚያበረታታና ሀብት በጥቂቶች እጅ እንዲሆን የሚያቀነቅን የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ነው። በአሜሪካና አብዛኞቹ የአውሮፓ ሃገሮች /ምዕራባውያን ሃገሮች/ የሚተገበር የፖለቲካ አመለካከት ነው።

የሠራተኛውን መደብ ሐሳብ የሚጋሩ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ቡድኖች በ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ እንደ አሸን መፍላት ጀመሩ። ይሁን እንጂ ቡድኖቹ የፈረጠመ ሀብት በፈጠሩት ካፒታሊስቶችና ከበርቴዎች እየተደቆሱ ውጤታማ መሆን አልቻሉም። እንዲያውም አንዳንዶቹ ቡድኖችና የሠራተኛ ማኅበራት እየተገለበጡ የባለሀብቱ በትር ሆነው ሠራተኛውን መደብ መምታት ጀመሩ። በዚህ የተቆጣው ሠራተኛው መደብ ከሶሻሊዝም ወደ ሥርዓት አልበኝነት (አናርኪዝም) ማጋደል ጀመረ። ሥርዓት አልበኝነቱ ደግሞ የኢንዱስትሪ ባለቤቶችን በኃይል አስወግዶ ኢንዱስትሪውን እስከ መቆጣጠርና መንግሥታትን እስከማስወገድ ድረስ የሚዘልቅ እንዲሆን የሠራተኛው መደብ ፈለገ። በዚህም ፖለቲካዊ አካሄዶችን በኃይል በመገርሰስ ላይ ተጠመዱ፤ የሠራተኛ ማኅበራትና የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኞችም የሠራተኛውን መደብ ተጠግተው ነገሮችን ማቀጣጠል ጀመሩ። በዚህም የሠራተኛው መደብ ጥያቄ ፖለቲካ እንዲያዝል ተደረገ።

ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ ነው እንግዲህ ሚያዝያ 23 ቀን 1878 ዓ.ም የተደራጁ ነጋዴዎችና ሠራተኞች «ፌዴሬሽን» የተሰኘ ድርጅት አንድ ሠራተኛ መሥራት ያለበት በቀን ስምንት ሰዓት ብቻ እንዲሆን አወጁ። ይሁን እንጂ አሠሪዎች ይህንን ውሳኔ በፀጋ መቀበል አልፈለጉም።

ሠራተኞቹ ደግሞ በሥራ ማቆም አድማና በሰላማዊ ሰልፎች መብታቸውን ለማስከበር ጥረታቸውን ቀጠሉ። በመጀመሪያ ተራማጆችና ሥርዓት አልበኝነትን አቀንቃኞች አመጽ ለማካሄድም ሆነ አሠሪዎችን ለማስገደድ ተቸገሩ። ይሄኔ ሳሙኤል ፊልድማን የተባለ ግለሰብ ሥርዓት አልበኝነትን በሚያቀነቅኑት ቡድኖች ጋዜጣ ላይ «በቀን ስምንት ሰዓትም ሠራ አስር ሰዓት ባሪያ ባሪያ ነው» ሲል አንድ ጽሑፍ አሳተመ። ይህን ተከትሎ ሩብ ሚሊዮን የሚሆኑ ሠራተኞችና ነውጠኞች የሥራ ሰዓት በቀን ስምንት ሰዓት ብቻ እንዲሆን በመጠየቅ በአሜሪካ ችካጎ ከፍተኛ ተቃውሞ ማካሄድ ጀመሩ።

በዚህም ተቃውሞ ነጋዴዎች፣ የሠራተኞች ማኅበራት፣ የሶሻሊስት ሌበር ፓርቲ እና የሠራተኛው መደብ ተሟጋቾች ንቁ ተሳታፊዎች ሆኑ። አመጹን ለመቀልበስ ክንዳቸው የዛለባቸው ከበርቴዎች እጅ ሰጡ፤ የሠራተኞች የሥራ ግዴታ በቀን ስምንት ሰዓት ብቻ እንዲሆን ወስነናል አሉ። በትግሉ ውስጥ ከሠራተኛው መደብ ጎን የነበሩት ነውጠኛ ተራማጆች ድሉን ከሥራ ሰዓት ማስቀነስ በላይም ስኬታማ እንዲሆን አደረጉት። በምጣኔ ሀብታዊ መዋቅሩ ውስጥም ለውጥ እንዲደረግ በመሻት ከሚያዝያ 23 ቀን 1878 ዓ.ም ቀጥሎ ያሉትን እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሰነዶችን ለሕትመት አበቁ።

ይህን የሠራተኞች ቀን ለማስከበር፤ ሠራተኛው ታገል፤ ጦርነት በገዥዎች ላይ፣ ሠላም በሠራተኛው መደብ ዘንድ ይስፈን፤ ሞት ለቅንጡዎችና ቦዘኔዎች፤ የደመወዝ አከፋፈል ሥርዓቱ ዓለምን ኢ-ፍትሐዊ አድርጓታል፤ አሠሪዎች በትንሽ ደመወዝ ጉልበት አይበዝብዙ፤ ወይም እነሱም ሠርተው እኩል ይከፈላቸው፤ መሥራት ወይም መሞት ምርጫቸው ይሁን፤ ፈንጅዎች ከምርጫ ኮሮጆ በተሻለ መብትን ያስከብራሉ፤ ፍላጎታችሁ ስምንት ሰዓት ማሠራት ይሁን፤ ካልሆነ የከበርቴዎችን ፖሊስና ሚሊሻ ጭምር ልክ እናስገባለን... የሚሉ መፈክሮችን በመያዝ አመጾች ተቀጣጠሉ።

ይህን ሁሉ ውጣ ውረድ አልፎ ሚያዝያ 23 ቀን 1878 ዓ.ም በመላው የተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች በ13 ሺህ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ከ300 ሺህ በላይ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ መቱ። በችካጎ ብቻ 40ሺህ ያህል ሠራተኞች ከፖሊስ ጋር የተፋጠጡ ነውጠኞችን ተቀላቀሉ። ነውጠኞቹ የሠራተኞችን መብት ለማስከበር ከበርቴዎችንና ገዥዎችን እስከወዲያኛው ለመፋለም እየተነሱ መደስኮር ቀጠሉ። ሠራተኞች እንደ ከበርቴዎች ክቡር ሰው መሆናቸውን «እናውጃለን» አሉ።

ይህን በተመለከተ በወቅቱ አልበርት ፓርሰንስ፣ ጆን ሞስት፣ አገስት ስፒስ እና ሉዊስ ሊንግ የተባሉ የመደቡ መብት አቀንቃኞች ስማቸው በሰፊው ይነሳ ነበር። በእነዚህ ሰዎች አርዓያነትም በችካጎና በመላው የተባበሩት አሜሪካ ግዛቶች ሰልፎች የሥራ ማቆም አድማዎች አቀጣጠሉ። መልካሙ ነገር ግን በሰልፎቹና አድማዎቹ እንደተፈራው የሰው ሕይወት አልተነጠቀም። ባለስልጣናትና ከበርቴዎች በሰልፎቹ የሠራተኛውን መደብ ጥንካሬና የነውጠኞችን ከሠራተኛው መደብ መሰለፍ በቅጡ ተረዱት። ሠራተኞችም አመጹን እየተቀላቀሉ ሄዱ፤ የሰልፈኞች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመቶ ሺዎች መሆን ጀመረ።

ሚያዝያ 25 ቀን 1878 ዓ.ም ግን በሰልፈኞችና አመጸኞች መካከል ግጭት ተፈጠረ። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ለስድስት ወራት ያህል ፖሊስ ሠራተኞችን በየጉራንጉሩ እያፈነ ወስዶ ማሰቃየትና ማሰር ጀመረ። አብዛኞቹ እስረኞች የነውጠኞቹ ደጋፊዎች የሆኑ የብረታ ብረት ሠራተኞች ማኅበር አባላት ነበሩ።

ይሁን እንጂ ይህም አካሄድ አመጹን መግታት አልቻለም፤ የብረታ ብረት ሠራተኞች በታሠሩበት አካባቢ በተደረገ አንድ የቅስቀሳ ንግግር ወደ 200 መቶ የሚጠጉ ሠራተኞች በአንድ ጊዜ ከፖሊስ ጋር ገጠሙ። ሁለት ሠራተኞች ሲሞቱ በርካቶች ቆሰሉ። ነውጠኞቹ ሕዝቡን ከጎናቸው አሰልፈው ከፖሊስ ጋር ለመፋለም በችካጎው ሀይማርኬት አደባባይ ስብሰባ ጠሩ። ነገር ግን በዕለቱ በነበረው የአየር ሁኔታ ምቹ አለመሆንና በማስታወቂያ ጊዜው ማጠር የተነሳ አስር ሺዎች ይካፈላሉ ተብለው ሲጠበቁ ሦስት ሺህ ሰዎች ብቻ ተገኙ። ከተገኙት ሰልፈኞች መካከል የችካጎ ከተማ ከንቲባ እስከ ቤተሰባቸው ተጠቃሽ ናቸው። በሰልፉ ላይ ንግግር ያደረገው አገስት ስፒስ «በማንም ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ አይገባም» በማለትም ከንቲባው ጥቃት እንዳይደርስባቸውና ከሠራተኛው ወገን መሰለፋቸውንም ተናገሩ።

ይሁን እንጂ ስፒስ ንግግሩን እየቀጠለ ሲሄድ ስሜት ቀስቃሽ ቃላትን መጠቀም ጀመረ። ይሄኔ ድንገት ሁለት ሠራተኞች ወደ ፖሊስ ተንደርድረው ሄዱ፤ ፖሊስም በአጸፋ ወደ ሰልፈኞቹ ተጠጋ።

ወዲያውኑ በፖሊስ ላይ ከማን እንደሆነ ያልታወቀ ቦንብ ተወረወረ። ነውጠኞች እንደተናገሩት ግን ቦንቡን የወረወረው የፖሊስ ደጋፊ የሆነ ሰው ነበር፤ ፖሊስ የኃይል እርምጃ ለመውሰድና ሠልፈኞችን እንዲመታ በር ለመክፈት። የሆነው ሆኖ ፖሊስ በወሰደው የአጸፋ ተኩስ ቢያንስ ስምንት ሰልፈኞች ሞቱ፣ አርባ ያህል ደግሞ ቆሰሉ። በተወረወረው ቦንብ የሞተው ግን አንድ ፖሊስ ብቻ ነበር።

በእርግጥ ቦንብ የወረወረው ሰው ማንነት በቅጡ አልተለየም ነበር፤ ነገር ግን የነውጠኞች መሪዎች የተባሉ ሰዎች ማለትም አልበርት ፓርሰን፣ አገስት ስፒስ፣ ሚካኤል ሺዋብ፣ ጆርጅ ኢንግል፣ አዶልፍ ፊሸር እና ሉይስ ሊንግ ታሠሩ። ለግድያውም ኃላፊነት አለባቸው ተባሉ። ከእስረኞቹ ሦስቱ ቦንብ በተወረወረበት ሰልፍ እንኳ ያልነበሩ ናቸው። ይህም ዓለም የእነዚህን ሰዎች መታሠር በተለየ ሁኔታ እንዲመለከተው አስገደደ፤ የታሠሩት በፖለቲካዊ አመለካታቸውና ማኅበራዊ ኢ-ፍትሐዊነትን በመታገላቸው ነው የሚል ዕይታ ተፈጠረ።

መስከረም 1 ቀን 1880 ዓ.ም ከእስረኞቹ መካከል ፓርሰን፣ ስፒስ፣ ኢንግል እና ፊሸር የተባሉት የሠራተኛው መደብ አቀንቃኞች በስቅላት ተቀጡ። ሊዊስ ሊንግ የተባለው ተሟጋች ደግሞ በመጨረሻ በባለስልጣናት እንደሚገደል ሲያውቅ ራሱን አጠፋ። ቀሪዎቹ የመብት ተሟጋቾች መሪዎች ፊልደን ኒቤ እና ሽዋብ ነበሩ፤ እነሱም ከስድስት ዓመታት እሥር በኋላ ነበር የተፈቱት።

በዚህ መልኩ በአሜሪካ የተቀጣጠለው ትግል ሚያዝያ 23 ቀን 1880 ዓ.ም የመጨረሻ ምዕራፍ አገኘ። በመንግሥትና በአሠሪ ከበርቴዎች ሰዎች በቀን ለስምንት ሰዓታት ብቻ መሥራት እንዳለባቸው ታመነ፤ ተወሰነ። ቅዳሜም እንደ እሑድ ሁሉ የሳምንቱ የእረፍት ቀን ሆነ። በዚህ የተነሳ ሚያዝያ 23 ቀን በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ደግሞ ግንቦት አንድ ቀን የዓለም የሠራተኞች ቀን እየተባለ ለሠራተኞች መብት ሕይወት የከፈሉ ሰዎች የሚታሰቡበት ሆነ።

በዓሉ በዚህ ዘመን በዓለም በብዙ ሃገራት እየተከበረ ይገኛል። በዓለማችን ከ66 ሃገራት በላይ ብሔራዊ በዓል አድርገው ያከብሩታል፤ ሌሎች ደግሞ ብሔራዊ በዓል ባያደርጉትም አስበውት ይውላሉ። ከፍተኛ የሠራተኞች ተጋድሎ የተካሄደባት አሜሪካ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ከታሪክ እንዲፋቅ ጥረት ታደርግ ነበር፤ በኋላ ግን አልቻለችምና እንዲሁ አስባው ትውላለች።

በኢትዮጵያ ደግሞ በተለይም በሶሻሊስቱ የደርግ መንግሥት ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠው ነበር፤ ምክንያቱም ደርግ ፊውዳላዊ ሥርዓትን ገርስሶ የሶሻሊስት ሥርዓት ስለሚከተል የሠራተኛው መደብ አከባሪ ነበር። ይህ ሠራተኞች ቀን በሃገራችን ሥራ ዝግ ተደርጎ ዛሬም ይከበራል።

በደርግ ዘመን ታላላቅ ሰልፎችና የተለያዩ መድረኮችን በማካሄድ ሲከበር የነበረ ሲሆን፣ እሱን አስወግዶ ወደ መንግሥታዊ ስልጣን ከመጣው የኢሕአዴግ መንግስት ወዲህ በአዳራሽ ውይይቶች፣ በኢንዱስትሪ ሠራተኞች መካከል በሚደረጉ ስፖርታዊ ውድድሮች እየተከበረ ይገኛል።

በሃገራችን ቀኑ በብሔራዊ ደረጃ ዝግ ተደርጓል። ከሃገራዊ ለውጡ ወዲህም በተለያዩ የሠራተኞች ጥያቄዎች ላይ ምክክር በማድረግ ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው ድምፃቸውን በማሰማት ያከብሩታል፤ ዛሬም የሠራተኞች የደሞዝ ጉዳይ፣በአሠሪና ሠራተኛ መካከል ያሉ አለመግባባቶች፣ የሥራ ደህንነት የሠራተኛውን የማኅበሮቹ አንጠብጋቢ ጉዳዮች እንደመሆናቸው በእዚህ ላይ የመወያያ ሰነዶች እየቀረቡ ውይይት በማድረግ ሲከበር ቆይቷል። የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን የሚያካሂዳቸው የሠራተኛው ስፖርታዊ ውድድሮችም ሌሎች የበዓሉ ድምቀት ሆነው ቀጥለዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

የዝነኞች ገጽ

ዘነቡ ገሰሰ - የራስ ቴአትር አምባሳደር

አቤል ገ/ ኪዳን

ስለ ራስ ቴአትር ስታወራ ስሜታዊ ትሆናለች። ቤቱን ትወደዋለች። ከሕይወቷ አብዛኛውን ክፍል የሙያዋን ደግሞ ሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ያሳለፈችበት ቤትም ነው። ራስ ቴአትር የፍቅር ቤት ነው ብላ ነው ማውጋት የምትጀምረው። ይህንንም ሁሉንም ቃለ መጠይቆቿን አይቶ ማረጋገጥ ይቻላል። እድሜዋን በሙሉ ስለኖረችበት እና ስለምታፈቅረው ራስ ቴአትር አውርታ የማትጠግበውን ዝነኛዋ ተዋናይ ፤ ተወዛዋዥ እና ድምጻዊ ዘነቡ ገሰሰ የራስ ቴአትር አምባሳደር ብለን ሰይመን ወጋችንን እንጀምር።

አባቷ የሸሬ ተወላጁ አስር አለቃ ገሰሰ ነጋሽ ናቸው። እናቷ ደግሞ የጎጃም ተወላጂ ወ/ሮ ስመኝ ሸለሙ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ጎንደር ጎርጎራ ላይ ተቀራረቡ። ትዳር ተመሰረተ ፤ ልጆችም ተወለዱ። ከተወለዱት ልጆች መካከል ደግሞ አንዷ ዘነቡ ነበረች።

የተወለደችው ሚያዝያ 27 ቀን 1956 ዓ.ም ነው። ጎርጎራ ላይ እትብቷ የተቀበረው ዘነቡ ገና የ3 ወር ልጅ እያለች ነበር ወደ አዲስ አበባ በወላጆቿ እቅፍ የመጣችው። ማረፊያዋም የጠቢባን መፍለቂያ የሆነችው ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ሆነ።

ልጅነቷ እንደማንኛውም ልጅ ነበር። ነገር ግን ነጻነት እና ሥነ ሥርዓት ሚዛን ጠብቀው የሚሄዱበት ቤት ውስጥ ነው ያደገችው። አባቷ ወታደር እንደመሆናቸው መጠን ቆፍጣና እና ሥርዓት ወዳድ ናቸው። ያም ቢሆን በተፈጥሮዋ መልከ መልካም እና ፍልቅልቅ ለሆነችው ልጃቸው ራሷን የምትገልጽበትን ነጻነት አልነፈጉም።

ቤት ውስጥ ያለው ነጻነት ግን ደጅ አልነበረም። ወቅቱ በደርግ እና በኢሕአፓ መካከል የከተማ ጦርነት የጦፈበት እና ወጣት በየጎዳናው ተገድሎ የሚታይበት ወቅት ነው። ይህ ጦስ ቀስ ብሎ እነ ዘነቡ ቤትም ደረሰ። አንዱ የዚህ የከተማ ሽብር ሰለባ ሆነ።

ይህ ኃዘን አፍላዋን ዘነቡን ክፉኛ አሳዘናት። ስለዚህም ይህን ኃዘን ለመወጣት መንገዶችን መፈለግ ያዘች። ሁነኛ መንገድ የሆነላት ደግሞ ሙዚቃ ማጉነራጎር ነበር። የዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ተማሪ የነበረችው ዘነቡ በተለይም የታጋይ ድምጽ ይጮህል የሚለውን የትግል መዝሙር ትወደውና አብዝታም ትጫወተው ነበር።

አንድ ቀን በትምህርት ቤቷ ይህን ሙዚቃ መድረክ ላይ ስትጫወት አንድ ሰው ሰማት። የሰማት ሰው ደግሞ ሻምበል ዮናስ የሚባል መልማይ ነበር። ዘፋኝ መሆን ትፈልጊያለሽ ወይ ብሎ ዘነቡን ጠየቃት። ሳታቅማማ አዎ አለች። ለአባት እና እናቷ አንዲትም ቃል ሳትተነፍስ ጓዟን ጠቅልላ የሰሜን እዝ ሰሜን ነጻብራቅ ኦርኬስትራን ተቀላቀለች ፤ ጉዞዋም ወደ አስመራ ሆነ። ለቤተሰቦቿ አስመራ ከደረሰች በኋላ ደወለች። አባት አዘኑ።

መልከ መልካሟ ዘነቡ ድምጻዊ ሆና የጀመረችው የጥበብ ሕይወት ብዙ አልገፋም። አንድ ቀን ከከረን ወደ አስመራ በመኪና ስትጓዝ ጉሮሮዋ ተዘጋ። ጊዜያዊ መዘጋት ቢመስልም አልስተካከል አለ። ይህን ተከትሎም ሙዚቃና ዘነቡ ተለያዩ።

ለሙዚቃ የተዘጋ ድምጽ ግን ለመድረክ ትወና እንዲሆን ሆኖ ተስተካከለ። ዘነቡ ከድምጻዊነት ብትለያይም በውዝዋዜ እና ባላት መልካም ቁመና የተነሳ የማርሽ ባንዱ ዘንግ ወርዋሪ በመሆን ሥራዋን ቀጠለች።

እዚህም ላይ አዲስ ክስተት ተፈጠረ። የ22 አመቷ ወጣት ዘነቡ ታደሰ የመጀመሪያ ልጇን ወለደች። በወቅቱ ደግሞ የሠራዊቱ አባል ሆኖ ልጅ መውለድ አይቻልምና ሕግ በመጣሷ ከሥራዋ ታገደች። ከብዙ ክርክር በኋላ ልጅ መውለድ ተፈቀደ። ልጇን እያሳደግች እያለ በቀይ ኮከብ ዘመቻ አባቷ ከመሐል ሃገር ወደ ምጽዋ መጡ ፤ እሷም ሥራዎችን ለማቅረብ ከባንዷ ጋር ምጽዋ ተገኘች። አባትና ልጅ ተገናኙ። ግጥምጥሞሹ ፊልም ይመስል ነበር ትላለች።

አባት እሷን ካገኙ በኋላ ግን ሳይነግሯት ወደ

አርቲስት ዘነቡ ገሠሠ፤

አስመራ ጠፍተው ገሰገሱ። ወደዚያ የሄዱት ለአንድ ዓላማ ብቻ ነበር። የልጅ ልጃቸውን ለማየት። የልጅ ልጃቸውን አይተው እና መርቀው ወደ ግንባር ተመለሱ። ከ10 ቀን በኋላ በውጊያ ላይ ተሰው።

አስር አለቃ ገሰሰ ልጃቸው መደበኛ ሕይወት እንዲኖራት ይፈልጉ ነበር። ስለዚህም ልጇን ይዛ ወደ አዲስ አበባ እንድትመለስ ይፈልጉ ነበር። ዘነቡ ሁለተኛ ልጅ ስትወልድ ሰራዊቱ አሰናበታት። ከ4 ዓመት ተኩል የሰሜን ቆይታ በኋላ ወደ አዲስ አበባ የተመለሰችው ዘነቡ በወታደር ቤት ኑሮ እና ልጅ በማሳደግ ተጎድታ ነበር።

ይህን ያየችው በሲኒማ ቤቶች አስተዳደር የራስ ሲኒማ ኃላፊዋ እመቤት ወልደ ገብርኤል አዘነች። ራስ ቴአትር የሥራ ማስታወቂያ ሲያወጣም መጥታ እንድትወዳደር ዘነቡን ጠራቻት። ነገር ግን ዘነቡ ብቸኛ ተወዳዳሪ አልነበረችም። 600 ያህል ተፎካካሪዎች ነበሯት። ፈታኙ ደግሞ ዝነኛው ተስፋዬ ለማ ነበር። የተጎሳቆለችውን ዘነቡ በአይኑ ቢያይም በውድድሩ ግን ተሰጥኦዋ በልጦ ታየው።

ተወዳዳሪዎቿን በልጣ ማለፏ ሲነገርም ቆይ ዝም በሉ የሁለት ወር ደሞዝ ስትበላ መልኳም ይመለሳል አለ። በ97 ብር ደሞዝ በ1976 ዓ.ም ራስ ቴአትርን ተቀላቀለች። ድምጻዊነቱ ቀድሞ ቀርቷልና የተቀላቀለቸው በተወዛዋዥነት ነበር። በወቅቱ ደግሞ ራስ ቴአትር የከዋክብቱ መናኸሪያ ነበረ፤ ሱራፌል አበበ ፤ አስቴር ከበደ ፤ ንዋይ ደበበ፤ ጸሐዬ ዮሐንስ ፤ አበበች ደራራ ፤ ኤልያስ ተባበል እና ሌሎችም የራስ ቴአትር ተቀጣሪዎች ነበሩ። ዘነቡ ከነዚህ ከዋክብት መካከል አንዷ ነበረች።

1981 ላይ በዘነቡ ሕይወት ላይ ሌላ እጥፋት/ ተርን/ ተከሰተ። ከድምጻዊነት ወደ ተወዛዋዥነት በድምጽ መዘጋት ምክንያት የዞረችው ዘነቡ አሁን ደግሞ ከውዝዋዜ ወደ ትወና ፊቷን ልታዞር ግድ ሆነ። ምክንያቱ ደግሞ በወቅቱ ኮከብ የነበረችው እንዬ ታከለ እና ጓደኞቿ የወቅቱ መሪ የነበሩት ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ጠይቀው በወቅቱ በሃገር ባህል ውዝዋዜ ዝነኛ የነበረውን ራስ ቴአትርን እንዲቀላቀሉ መደረጉ ነው።

አዳዲሶቹ ተወዛዋዦች ሲመጡ የዘነቡ እና ውዝዋዜ ውዳጅነት ተጠናቀቀ። ውዝዋዜ መድረኩን ለወጣቶቹ ለቅቃ የትወናውን መድረክ ተቀላቀለች። በትወናው በርካታ የመድረክ ተውኔቶችን የሠራች ሲሆን ከነዚህም መሀከል ላጤ ፤የሰው ሰው፤ ዘር አዳኝ ፤ አሻራ ተጠቃሽ ናቸው። ከትወናው በተጨማሪም ግን ዘነቡ የምትወደውን ራስ ቴአትር በሜክ አፕ አርቲስትነት ፤ አልባሳት እና ቁሳቁስ ኃላፊነት ፤ በአዳራሽ ኃላፊነት እና ሌሎችም ዘርፎች ሰርታለች።

ከመድረክ ተዋናይነት በኋላ ወደ ፊልም ሥራም የተቀላቀለችው ዘነቡ ታዋቂ የሆነችበትን ሹገር ማሚ ፊልም ጨምሮ አያስቅም ፤ አለሜ፤ ኤሽታኦል ፤ ያለ ሴት ፤ አስታራቂ ፤ መፈንቅለ ሴቶች እና ሌሎች በርካታ ፊልሞች ላይ ተውናለች። በጉማ የሽልማት ሥነ ሥርዓት ላይ በምርጥ ረዳት ተዋናይት ዘርፍ በትህትና ፊልም አሸናፊም ሆናለች። በማስታወቂያውም ታዋቂ የሆነው የቆርቆሮ ማስታወቂያ ጠብ ሲል ስደፍን የሠራች ሲሆን የሙዚቃ ቪዲዮዎችም ላይ ተሳታፊ ሆናለች።

የ2 ወንድ 2 ሴት ልጆች እናት እንዲሁም የ 2 የልጅ ልጆች አያት የሆነችው ዘነቡ በእድሜዋ መጨረሻ ላይ በጡት ካንሰር ተጠቅታ በሕክምና ላይ ነበረች። በዚህ የተነሳም በመገናኛ ብዙኃን በተደጋጋሚ የቀረበች ሲሆን ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ሴቶች በጡታቸው ዙሪያ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ስትመክር እና ሃገር ሰላም እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ስታሳስብ ኖራለች። እሷ እንዲያ ትበል እንጂ በተለይ በዩቲዩብ እሷን አስመልክቶ የሚነዙት አሉባልታዎች ቀላል አልነበሩም። በተደጋጋሚ ሞታለች እና ድናለች የሚሉ አላስፈላጊ አሉባልታዎች ዘነቡን እና መላ ቤተሰቧን ረፍት ሲነሱ ከርመዋል።

ከእለተ ዕረፍቷ በኋላ በምትወደው ራስ ቴአትር እሷን ለመዘከር በተዘጋጀ መርሐ ግብር ላይ ወዳጆቿ ስለ እሷ ብዙ የተናገሩ ሲሆን ከነዚህም መሐከል ራስ ቴአትር እንድትቀጠር ትልቁን ድርሻ የተወጣችው አርቲስት እመቤት ወልደ ገብርኤል በሲቃ የዘነቡን ልጆች በመንከባከብ ለሷ ያለንን ፍቅር እንግለጽ ስትል ጥሪ አቅርባለች።

ሌላኛው የጥበበ ሰው ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ በበኩሉ የዘነቡን ሕይወት እና ባህሪ አወድሷል። የዩኒቨርሲቲ የ4ኛ አመት ተማሪ እያለሁ ራስ ቴአትር ስመጣ ተቀብላ በፈገግታ ያስተናገደችኝ እና ባይተዋርነት እንዳይሰማኝ ያደረገችኝ እሷ ናት ብሏል ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ። ለጥበብ ካላት ጽኑ ፍቅር የተነሳ ብዙ መስዋዕትነት በመክፈል ከቀደምት የሙያ አባቶቿ እነ ዮፍታሄ ንጉሴ ጋር እንደምትመሳሰል የተናገረው ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ዘነቡ ብትቸገር እንኳን አማራሪ ሳትሆን አመስጋኝ እንደነበረች እንዲሁም የሁልጊዜ ሀሳቧ የምትወደው ራስ ቴአትር አድጎ ማየት እንደነበር ተናግሯል።

በእርግጥም ለጥበብ እና ለራስ ቴአትር ባላት ፍቅር ብቻ ሃገሯን ስታገለግል የኖረችው ዘነቡ ይህን ሁሉ ዘመን ስታገለግል ደሞዟ ሁለት ሺ አምስት መቶ ገደማ የነበረ ሲሆን ኑሮዋም የምቾት የሚባል አልነበረም።መኖሪያ ቤት እንኳን ለብዙ ጊዜ ያልነበራት ሲሆን በቅርቡ ኢንጂነር ታከለ ኡማ ከንቲባ በነበሩበት ወቅት በእጣ መኖሪያ እንዲደርሳቸው ከተደረጉ አርቲስቶች መሐከል አንዷ በመሆኗ ነበር የራሷ ቤት የኖራት። እንዲያም ቢሆን ግን በብዙዎች ፊት ላይ ፈገግታን እየዘራች የመድረክ ድምቀት እና የታላቁ ራስ ቴአትር አምባሳደር እንደሆነች እስከህይወቷ መጨረሻ ዘልቃለች።

ነፍስ ሄር ዘነቡ ገሰሰ!

የአጠናን ዘዴ ለልጆች

አስናቀ ፀጋዬ

ልጆች እንዴት ናችሁ? ሳምንቱስ እንዴት አለፈ? ዓመት በዓልስ እንዴት ነበር? ጥሩ ነበር? ያው ልጆች ዓመት በዓል አልፎ በዚህ ሳምንት ትምህርት ጀምራችኋል። የሁለተኛ መንፈቅ ዓመት ትምህርት ሊጠናቀቅ ደግሞ የቀሩት ግዜያት ጥቂት ናቸው። ታዲያ ልጆች በነዚህ ግዜያት በርትታችሁ መማርና ማጥናት ይኖርባችኋል። ያልገባችሁ ትምህርት ካለ ደግሞ መምህራኖቻችሁን፣ ወላጆቻችሁንና አስጠኚዎቻችሁን መጠየቅ አለባችሁ።

ልጆች ለመሆኑ እናንተ በምን አይነት መንገድ ነው የምታጠኑት? በትምህርታችሁ የተሻለ ውጤት ለማምጣትስ የተለየ የአጠናን ዘዴ ትከተላላችሁ? መቼም መልሳችሁ «አዎ» እንደሚሆን አልጠራጠርም።

ሁሉም ልጆች የሚመቻቸውንና ለውጤት የሚበቃቸው የአጠናን ስልቶችን ይከተላሉ። በተመሳሳይ ወላጆችም ልጆቻቸው የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ በተለያየ መንገድ ልጆቻቸውን ያስጠናሉ። እናንተም የራሳችሁ የሆነ የአጠናን ስልት ሊኖራችሁ እንደሚችል እገምታለሁ።

ይሁን እንጂ በአብዛኛው ተማሪዎች በጥናት የሚጠመዱት በፈተና ወቅት እንጂ በመደበኛው የትምህርት ወቅት አይደለም። ወላጆችም በብዛት ልጆቻቸውን ሲያስጠኑ የሚታዩት በዚሁ የፈተና ወቅት ነው። ይህ ባለመሆኑ ታዲያ ልጆች በፈተና ወቅት ብቻ ሳይሆን በሌላ ግዜም ማጥናት አለባችሁ። ወላጆችም ልጆቻችሁን ዘወትር ማስጠናት ይጠበቅባቸኋል።

ማንም ቢሆን እንዴት ማጥናት እንዳለበት አውቆ የተወለደ የለም። ለዚህም ልጆች የተወሰኑ የማጥናት ክህሎቶችን መማርና መለማመድ ያለባችሁ። ይህም ትምህርታችሁን በቀላሉ ለመከታተልና በክፍል ውስጥም ጥሩ አፈፃፀም እንዲኖራችሁ ያስችላችኋል።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትና ትምህርትን በተሻለ ሁኔታ ለማጥናት የሚያስችሉ ስድስት ደረጃዎች ናቸው ። እናንተም ልጆች እነዚህን ስድስት ደረጃዎች ተግባራዊ በማድረግ ብታጠኑ በትምህርታችሁ የተሻለ ውጤት እንደምታመጡ ተስፋ አደርጋለሁ።

1ኛ፡-ትኩረት አድርጉ፤ጥሩ ጥናት የሚጀምረውም በክፍል ውስጥ ነው!

መምህራኖቻችሁ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ በትኩረት የምትከታተሉና ማስታወሻ የምትይዙ ከሆነ የመማርና የማጥናት ሂደት ውስጥ ገብታችኋል ማለት ነው። ለዚህም ታዲያ ትኩረታችሁን ከሚስቡ ነገሮች ራቁ። በተቻለ አቅም ከፊት ለፊት በመቀመጥ ትኩረታችሁን በመሰብሰብ ትምህርታችሁን ለመከታተል ጥረት አድርጉ።

2ኛ፡- ማስታወሻ ያዙ፤ የጥናት ቀሳሱ መንገድ ነው!

በክፍል ውስጥ መምህራኖቻችሁ ሲያስተምሩ የሚዘረዝሯቸውን እውነታዎችንና በሰሌዳ ላይ የሚጽፏቸውን ነጥቦች ጻፏቸው። ማስታወሻችሁን በደብተራችሁ ላይ ስታሰፍሩ በጥሩ የእጅ ጽሑፍ ይሁን። ይህም በኋላ ላይ በቀላሉ ለማንበብ ያግዛችኋል። ማስታወሻዎቻችሁን በየትምህርት አይነቱ ለይታችሁ መያዝም አይከፋም።

3ኛ፡- አስቀድማችሁ አቅዱ

ለዓርብ ፈተና ለማጥናት እስከ ሐሙስ ምሽት ድረስ መጠበቅ ሞኝነት ነው። የተሻለ ውጤት ለማምጣትም አስቸጋሪ ይሆናል። ስለዚህ ከፈተና በፊት አስቀድሞ ማቀድና ማጥናት አስፈላጊ ነው።

የፈተናና የቤት ሥራ የተሰጠበትን ቀን መዝግባችሁ ያዙ። ይህም ከክፍል በኋላ በእያንዳንዱ ቀን ምን ምን

ማድረግ እንዳለባችሁና በእያንዳንዱ ርዕስ ላይ ምን ያህል ግዜ ማጥፋት እንዳለባችሁ ለማቀድ ይረዳችኋል።

4ኛ፡-ከፋፍላችሁ ስማጥናት ሞክሩ

የምታጠኑት ትምህርት በርከት ያለ ከሆነ በየትምህርት አይነቱና እንደየርዕሰ ጉዳዩ በመከፋፈል ነጣጥሎ ማጥናቱ ይጠቅማችኋል። ጠቅለል ባለው የትምህርት አይነት ላይ አተኩሮ ከማጥናት በውስጡ የያዘውን ርዕሰ ጉዳይ በመነጣጠል ማጥናቱ ይመረጣል።

ሌላኛው ትምህርትን ከፋፍሎ ለማጥናት የሚያግዘው መንገድ በየቀኑ ማጥናት ነው። ይህም ሁሌ ማስታወሻዎቻችሁን ለመከለስና የተማራችኋቸውን ምዕራፎች ለመቃኘት ያግዛችኋል።

5ኛ፡- ግርታ ከተፈጠረ እርዳታ ጠይቁ

የትምህርት መሣሪያውን በሚገባ ካልተረዳችሁ በአግባቡ ማጥናት አትችሉም። ያልገባችሁ ነገር ካለ መምህራኖቻችሁን ከመጠየቅ ወደኋላ አትበሉ። የተፈጠረውን ግርታ ማስታወሻዎቻችሁን ዳግም በማንበብም መፍታት ትችላላችሁ። በቤታችሁ ሆናችሁ ያልገባችሁ ነገር ካጋጠማችሁ ደግሞ ወላጆቻችሁን በመጠየቅ መረዳት ይቻላል።

6ኛ፡- በቂ እንቅልፍ ውሰዱ

እንበልና ፈተና ነገ ነው። እናንተ ደግሞ የጥናት እቅዳችሁን ተከትላላችሁ ለፈተናው ደርሳችኋል። ይሁንና በድንገት ያጠናችሁትን ላታስታወሱ ትችላላችሁ። ሁለት ሲደመር ሁለት ስንት እንደሆነ ሊጠፋባችሁም ይችላል። አትረበሹ ልጆች!

አዕምሯችሁ የሰጣችሁትን ሁሉንም መረጃዎች እስኪያጣጥም ድረስ ግዜ ይፈልጋል። ለአዕምሯችሁ እረፍት ከሰጣችሁትና ጥሩ እንቅልፍ ከወሰዳችሁ ታዲያ በጧት ወደ እናንተ በሚመጣው ነገር ትገረማላችሁ።

ስፖርት

አሳዛኙ የማራቶን ሽንፈት

ብርሃን ፈይሳ

ዘመኑ እአአ 1954 ነበር፤ የእንግሊዝ ዋና ከተማ በሆነችው ለንደን የኮመንዌልዝ የወንዶች ማራቶን ውድድር እየተካሄደ ነው። ቀዳሚው አትሌት ረጅሙን የጎዳና ላይ ሩጫ በአስደናቂ ብቃት ሸፍኖ ውድድሩ ወደሚጠናቀቅበት ስታዲየም ገብቷል። ርቀቱን ለማጠናቀቅም የ200 ሜትር ርቀት ብቻ ቀርቶታል።

በድንገት ግን አትሌቱ የመዳከም ሁኔታ አሳየ፤ ሩጫው ወደ እርምጃ ጥቂት ወደፊት ከዚያ ወደጎን ደግሞ ወደሁዋላ እያለ በመጨረሻ ራሱን ስቶ ወደቀ። ብርቱው አትሌት አሸናፊነቱን ሳያረጋግጥ በስታዲየም የተገኘው ስፖርት ወዳድም የናፈቁትን አስደናቂውን ብቃት ሊመለከቱ የማይችሉበት አሳዛኝ ክስተት ተፈጠረ። ይህ ታሪክ እንግሊዛዊው አትሌት ጂም ፒተርስ

የስፖርት ተግባር ማወዳደር እና ማፎካከር እንደመሆኑ ተሸናፊና አሸናፊ መኖሩ የግድ ነው። የተሻለው አካል አሸናፊ ሲሆን፤ በብቃቱ ደከም ብሎ የተገኘው ደግሞ የተሸናፊነት ጽዋን መጎንጨቱ የግድ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ግን በስፖርታዊ ውድድሮች አሳዛኝ የሚባሉ ተሸናፊዎች ይታያሉ። ተወዳጁን የእግር ኳስ ስፖርት እንደማሳያ ብናነሳ በጨዋታና በግብ ብልጫ ሲመራ የቆየው ቡድን በመጨረሻ ሰዓታት በሚቆጠርበት ግብ ተመትቶ ከውድድር ውጪ ሲሆን አሳዛኝ ተሸናፊ ይባላል። የዛሬው የስፖርት ማህደር ገጽ ደግሞ በአትሌቲክስ ስፖርት አሳዛኝ ከሆኑ ክስተቶች መካከል አንዱ የሆነውን የዚህን የጂም ፒተርስ ታሪክ ያወሳል።

ይህ አትሌት እአአ 1918 የተወለደ እንግሊዛዊ የረጅም ርቀት አትሌት ነው። በረጅም ርቀት አትሌት የጀመረ የሩጫ ሕይወቱ እንደሚጠበቀው ስኬታማ ባይሆንም ፊቱን የጎዳና ላይ ውድድር ወደሆነው ማራቶን ማዞሩ የስኬቱን መንገድ በግልጽ አመላክቶታል። በማራቶን የዓለም ክብረወሰን የሆነ ሰዓትን ከ2ሰዓት ከ20 ደቂቃ በታች በመግባት የግሉ በማድረግ አስደናቂ አቋሙን ያረጋገጠ አትሌት ነው። ይኸውም ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩት የማራቶን አትሌቶች ወደ አራት ደቂቃ የሚሆን ብልጫ ያለው ሲሆን፤ ይኸውም አትሌቱ የተለየ ተሰጥኦ ያለው መሆኑን ያመሳከረ ነበር።

የመጀመሪያውን ክብረወሰን እአአ በ1952 ያስመዘገበ ሲሆን፤ የገባበት ሰዓትም 2:20:42 ነበር። በቀጣዩ ዓመት በተካሄደ ሌላ ውድድር ላይ ደግሞ 2:18:40 በሆነ ሰዓት በመግባት የራሱን ክብረወሰን በማሻሻል በርካቶች ሊያደርጉት ቀርቶ ሊያስቡት የማይችሉትን ጀብድ ፈጸመ። ቀድሞ በመግባት አሸናፊ ከመሆን ባለፈ ፈጣን ሰዓትን ማስመዝገብ የቃኪክሩ አንድ አካል በሆነበት የአትሌቲክስ ስፖርት ሰከንዶችን ማሻሻል የሚያስገኘው ክብር ግልጽ ነው። በአንጻሩ ይህ አትሌት ደቂቃዎችን በማሻሻልም ጭምር የወቅቱ የማራቶን ቁጥር አንድ አትሌት ለመሆን ችሏል።

ብርቱው አትሌት ፒተርስ በዚያው ዓመት በሆላንድ በተካሄደ ውድድር ላይ በድጋሚ ሰዓቱን ለማሻሻል አቅዶ ቢሮጥም፤ 2:19:22 በሆነ ሰዓት ነበር የገባው። ይኸውም ሁለተኛው የማራቶን ፈጣን ሰዓት ነበር።

በቀጣዩ ዓመት የኮመን ዌልዝ ውድድር አትሌቱ ተሳታፊ ሲሆን፤ በተለመደው ብቃት ርቀቱን ከመሸፈን ባለፈ የራሱን የቀደመ ሰዓት በድጋሚ ሊያሻሽል እንደሚችልም ግልጽ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ በሁለተኛነት እርሱን ከሚከተለው አትሌት 17 ደቂቃዎችን አስቀድሞ በመሮጥ የጎዳና ላይ ሩጫውን አጠናቆ ወደ ስታዲየሙ መገስገስ ችሎ ነበር። በኢምፓየር ስታዲየም ውስጥም ተዓምረኛውን አትሌት ለመመልከት 35ሺ የሚሆኑ ተመልካቾች ተገኝተው ድጋፋቸውን ይሰጡ ነበር።

የተጠበቀው አትሌት በስታዲየሙ ብቻውን እየሮጠ፤ ሕዝቡም ደስታውን እየገለጠ ባለበት ሁኔታ ግን ድንገተኛ ክስተት ታየ። ይኸውም አትሌቱ በመልካም ጤንነት ላይ አለመሆኑን የሚያመላክት ሲሆን፤ ከመንገዳገድ አልፎ 200 ሜትር እየቀረው ተዝለፍልፎ ወደቀ። በቦታው የነበሩት የሕክምና ባለሙያዎችም ሕይወቱን ለማትረፍ ፒተርስን የሐኪም ድጋፍ እንዲያገኝ ተረባረቡ። ለሶስት ሰዓታት ራሱን ከሳተ በኋላ ቢነቃም በነበረበት አደገኛ ሁኔታ አንጻር በድጋሚ ግን ወደ ሩጫ ሕይወት ሊመለስ አልቻለም።

ውድድሩን ሙሉ ለሙሉ ባያጠናቅቅም የውድድር አዘጋጆቹ ተወያይተው ርቀቱን የሸፈነበት 2ሰዓት ከ17 ደቂቃ ከ39 ሰከንድ የሆነ ሰዓት ሶስተኛው ክብረወሰን ሆኖ ሊመዘገብለት ችሏል። አትሌቱ ጤናው ከተመለሰለት በኋላም ሕይወቱ የነበረበትን አደገኛ ሁኔታ «በዚያን ዕለት አለመሞቴ እድለኛ ስለነበርኩ ነው» በማለት ነበር የገለጸው።

ጠንካራው አትሌት ጂም ፒተርስ